# ለምን ዐይነት ህብረተሰብ ነው የምንታገለው ? ፍልስፍናችስ ምንድነው ?

## መግቢያ

ባለፉት 18 ዓመታት በአገራችን ቁጥራቸው የማይታወቁ ብዙ ፓርቲዎች እንደ አሸን ፈልቀዋል። ከዚህ በተረፈ ፣ መብታችን ይከበር ወይም ደግሞ የራሳችንን ዕድል በራሳችን መወሰን አለብን የሚሉ የብሄረ-ሰብ ድርጅቶች እዚህና እዚያ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛሉ። አብዛኛዎቹ ለዲሞክራሲ ፣ ለገበያ ኢኮኖሚና በአጭሩ ለሊበራል ዲሞክራሲ እንታገላለን ብለው እንደ አማራጭ ሊታዩ እንደሚችሉ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ሲያሰሙ ከርመዋል። አንዳንዳቹ ደግሞ ፣ እዚያው በዚያው የሊበራል ዲሞክራሲንና የነፃ ገበያን ተግባራዊ ለማድረግ ነው የምንታገለው እያሉ ፣ በሌላ ወገን ደግሞ ኢትዮጵያዊ አይደለሁም ፣ ስለዚህም ትግላችን ለነፃነት ነው ብለውና የኢትዮጵያን ብሄራዊ ነፃነትና የህብረተሰብ ዕድገት ከሚቀናቀኑና ህልውናዋን ለማናጋት ከሚታገሉ ጋር በመሰለፍ የተምታታ ፖለቲካ ሲያካሂዱ ይታያል። ይህ በእንደዚህ እያለ ፣ በተለይ የኢህአዴግ አምባገነናዊ አገዛዝ ፣ ለከፋፍለህ ግዛ ፖለቲካው እንዲያመቸው በብሄረ-ሰብ ነፃነት ስም አሳቦ ህብረተሰብአዊ ግጭትን ሊያሰክትል የሚችል የክልል ፖለቲካ መከተሉ ብዙዎችን እንዳስቆጣ የማይታበል ሀቅ ነው። በዚህም ምክንያት የፖለቲካው ትግል ከተራ የሊበራል ዲሞክራሲ አልፎ አገርን ከርስ በርስ ግጭት የሚያድንና የአገሪቱን አንድነት ለማሰጠበቅ  የሚካሄድ ትግል ለመሆኑ ግልጽ ሆኖ መታየት ከጀመረ ዐመታት አልፎታል። የአገዛዙ እልከኝነትና አገርን መፈራረስ  አስመርሮናል ያሉ ኃይሎች ደግሞ ፣ አገዛዙን ሰላምና ዲሞክራሲን ማስተማር አይቻልም ፤  በሰላምም ወደ ህዝባዊ መንግሰት መሸጋገር አይቻልም ፣ ያለው አማራጭ የጦር ትግል ብቻ ነው ብለው በየቦታው የትጥቅ ትግል የሚያካሂዱ ብሄራዊ ኃይሎች እንዳሉ ይታወቃል።

በተለይም ከምርጫ 1997 ዓ.ም በኋላ አገዛዙ ራሱ ላወጣውና  አምንበታለሁ ብሎ ለሚያሰተጋባው ህገ-መንግስት ተገዢ ለመሆን ፈቃደኛ ባለመሆኑና የህዝብንም ፍላጎት ለማሟላት ዝግጁ ለመሆን ባለመፈለጉ ፣ ፖለቲካዊ መፍትሄ እየደበዘዘ እንደመጣ መንግስት ከሚከተለው ፖለቲካ መገንዘብ ይቻላል። ይሁንና ፣ ይህም ሆኖ እያለ አሁንም ቢሆን የሰላሙ ትግል ተሟጦ አላለቀም ፤ ፋታ እንስጠው ፣ በህገ-መንግሰቱ ክልል ውስጥ እንታገል የሚሉ ኃይሎች እንዳሉ ግልጽ ነው። የአገዛዙ እልከኝነት ፣ በሆነው ባልሆነው እያሳበበ በሰላማዊ ትግል ብቻ እናምናለን ፤ ለዚህም ህገ-መንግስቱ በሚያዘው መሰረት እንታገላለን ብለው ቆርጠው የተነሱ ድርጅቶችን ንብረት ላይም ጉዳት እያደረሰና እንዳይደራጁ  መንገዱን ሁሉ  እየዘጋባቸው ነው ። በዚህም ምክንያት አገዛዙ  ፣ እኔ በራሃ ለበራሃ ተንከራትቼ ፣ ደሜን አፍስሼ የያዝኳትን ስልጣን በሰላም አለቅም ፤ ግብ ግብ እንጋጠምና ካሸነፋችሁ ብቻ ስልጣንንን መውሰድ ትችላላችሁ እያለ ለጦርነት እየጋበዘ ነው። የሰሞኑን አገርን ለውጭ ከበርቴዎች መሸጥና በግብዣ አገሬን ቅኝ አገዛዝ (Colonialism by Invitation) አድርጓት ብሎ ሸር ጉድ ማለቱ የሰላምን አርማ  አንግበን የምንታገለውን ሁሉ እያስቆጣ ነው። የአገዛዙን ባህርይ ለመረዳት ብቻ ሳይሆን በሚከተለው እጅና  እግር የሌለው ፖለቲካ ግራ የተጋባን ሰዎች ምን ዐይነት ፖለቲካ ብናካሂድ ይሻላል እያልን ከራሳችን ጋር ሙግት ውስጥ ገብተን የምንጨብጠውንና የምንይዘውን አጥተን በውዥንብር ዓለም ውስጥ እየዋኘን ነው።

ይህ በዚህ እንዳለ  ኢትዮጵያን ለማዳን  አማራጮቹ  እኛ ነን  ብለውና  ካለ  ሊበራል ዲሞክራሲ  የሚያዋጣ ነገር የለም ብለው የሚታገሉ ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የህብረት ያለህ እያሉ እየጮሁ እዚያው በዚያው ደግሞ ለህብረት እንቅፋት በመሆን የተምታታ ፖለቲካ  በማካሄድ  ግራ የሚያጋቡ ኃይሎች  የፖለቲካውን ትግል  ፈር እንዲስት  እያደረጉት ነው ። አንዳንዶቹ ደግሞ የርስ በርስ ሸኩቻ ውስጥ በመግባት ኃይልን  በመበታተንና  ሞራልን በማዳከም ሳይወዱ በግድ የገዢውን መደብ  የተደናበረ  ፖለቲካ  እያጠናከሩና እንዲገፋበት እያደረጉ ነው።  አብዛኛዎቹ ተቃዋሚ  ነን የሚሉ ኃይሎች  በቅንነትና  ወደ ውጭ ወጥተው  ለአገራችን  በሚበጀው  የፖለቲካና የኢኮኖሚ

እንዲሁም የማህበራዊ-ሰብ ጥያቄዎች ላይ በግልጽ ከመወያየት ይልቅ ፣ ህዝብ ውክልናን የሰጠን ለኛ ብቻ ነው በሚል የፖለቲካውን ፈር ከሳይንስና ከፍልስፍና በማራቅ በብዙ መቶ ሺህ የሚቆጠር ህዝብን ግራ እያጋቡ ነው። የፖለቲካው ውስጠ-ኃይል ሌላ መልክ እየያዘና ከቁጥጥር ውጭ በመውጣት መንፈስን እያዳከመ ነው። ከዚህም በላይ ፣ ፖለቲካን ለራሳቸው ጥቅም ለማድረግ የሚሯሯጡና የሞራል ብቃት የሌላቸው ፣ የሚንቀሳቀሱ ድርጅቶችን ጠጋ በማለት ወይም ደግሞ የራሳቸውን በመፍጠር ለውዥንብሩ ተጨማሪ እምርታ እየሰጡት ነው። የዚህ ሁሉ ችግር ምንድን ነው ? የየድርጅቶቹስ ፍልስፍና ምን ይመስላል? በእርግጥስ ድርጅቶቹ እንደ አማራጭ ሊቀርቡ ይችላሉ ወይ? የአገራችንን የተወሳሰበ ችግር በሊበራል ዲሞክረሲና በገበያ ኢኮኖሚ ሊፈቱ ይችላሉ ወይ ? ሊፈቱ የሚችሉ ከሆነ በዝርዝር ማስረዳት ይችላሉ ወይ ? እንዴትስ አድርገው በዚህ አማካይነት ብሄራዊ ኢኮኖሚና እርስ በርሱ የተሳሰረ ህብረተሰብ መገንባት ይችላሉ ? እነዚህን ነገሮች ከመተንተኔ በፊት ስላሉን ችግሮች እንወያይ።

## መሰረታዊ ችግራችን !

በተለይም ስልጣንን የችግር መፍቻ ከማድረግ ይልቅ መባለጊያና መጨቆኛ ያደረጉ ወይም የሚያደርጉ ኃይሎች ተነግረውና ተመክረው አልሰማ የሚሉ ከሆነ በተቀነባበረ መልክ መዋጋት እንደሚያስፈልግ በከፍተኛ ዕወቀት በተካኑ ቀሳውስትም የታመነበት ነው። ምክንያቱም ፣ ማንኛውም ግለሰብ በእግዚአብሄር አምላክ ምስል የተፈጠረ በመሆኑ ፣ አንድ መንግስት ወይም አገዛዝ የተፈጥሮን ህግ እየጣሰ ሰውን ማሰቃየት የለበትም ፤ ለስልጣኔ እንቅፋት በመሆን የታሪክን ሂደት ማጣመም የለበትም ከሚለው ተራ ሎጂክና የተፈጥሮ ህግ በመነሳት የተደረሰበት መደምደሚያ ነው። በታሪክ ውስጥ መሪዎችን ከአረመኔ ባህሪያቸው ለማላቀቅ በብዙ ፈላስፎችና የሊትሬቸር ሰዎች ተሞክሮ የከሸፈበትና እስከተወሰነ ደረጃም ድረስ በአመጽ ብቻ ወደ ነፃነት የተደረሰበት አገሮችን መጥቀስ ይቻላል። ጥያቄው የአመጽን ትግል እንደ አማራጭ የሚወስዱ ኃይሎች ዕውነተኛ ፍልስፍናን ይዘው ነው የሚታገሉት ወይ? ስልጣን ከያዙስ በኋላ ወደ ቂም በቀል አያመሩም ወይ? ታሪክ የሚያሰራና ህዝብን የሚያስማማ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ፖሊሲን ተግባራዊ በማድረግ የህዝብን ጥያቄና ፍላጎት መመለስና ማሟላት ይችላሉ ወይ ? የሚለው ነው ብዙ ጊዜ የሚያስቸግረው። እንደኛ ባለው ምሁራዊ እንቅስቃሴ በጠባብ አመለካከት በተመሰረተበት አገርና ፣ ሎጂክና አርቆ-አስተዋይነት የዕውቀት ምንጭ ሆነው በማይወሰዱበት ፣ አመፃዊ ትግል የግዴታ የሚፈለገውን ትግል አያመጣም። በተለይም ፣ በ20ኛው ክፍለ ዘመን የተካሄዱትንና ዛሬም የተካሄዱትን የጦርነት ትግሎች ለተመለከተ ፣ አንድ አምባገነናዊ አገዛዝ በሌላ ከመተካቱና ህዝቦችም የዓለም አቀፋዊ ኢንስቲቱሽኖች መጨፈሪያ ከመሆናቸው በስተቀር ዕውነተኛ ነጻነት ለመጎናጸፍ እንዳልቻሉ በእድሜያችን ዘመን ያረጋገጥነው ነው። ስለዚህም ከአንድ ስህተት ወደ ሌላ ላለማምራት ከተፈለገና የድህነትን ዘመን ለማራዘም ካልተፈለገ ማንኛውም ኃይል ሊከተለው የሚገባው መሰረተ-ሃሳብ አለ።

ለምን እንደሆን አይገባኝም በኛ አገር ያለው ትልቁ ችግር-በውጭው ዓለም ያለውንም ኢትዮጵያዊ ጨምሮ-ቲዎሪን ፣ ፍልስፍናንና ሳይንስን የመጥላት አዝማሚያው ከፍ ያለ ነው። በዚህም ምክንያት ፣ ብዙዎቻችን ጥያቄ እንዳንጠይቅ ፣ የአንድን ነገር አነሳስና ዕድገት ዞር ብለን እንዳናይና በተወሰነ ክልል ብቻ አስተሳሰባችንን በወፍራም ግድግዳ በማጠር ሌላ ሃሳብ ወደ ጭንቅላታችን ውስጥ እንዳይገባ ገድግደን ይዘናል። በዚህም ምክንያት ትግላችን ችግርን ሊፈታ በሚችል ሃሳብ ዙሪያ መሆኑ ቀርቶ ጥቂት ሰዎችን በማምለክና በተወሰኑ ነገሮች ላይ ፣ ግን ደግሞ የሚያሰለቹና ጭንቅላትን ገትረው በሚይዙ ላይ በማትኮር የትግሉ አድማስ እንዲጠብ እያደደረግን ነው። በየአገሮች የተካሄዱትን ትግሎች እንደልምድ በመውሰድና ፣ ህዝቦች የደረሱበትን ውጤት በማውረዳና በማውጣት አገናዝቦ የራሳችንን ግምገማ በመስጠት ወደ ትክክለኛው የትግል ስልት ለመድረስ ያለን ችሎታ እየመነመነ መጥቷል ብል የምሳሳት አይመስለኝም። ስለዚህም የየድርጅቶችንም ሆነ መሪ እንሆናለን የሚሉትን ግለሰቦች ሁኔታ ስንመለከት ፣ ትግላቸውም ሆነ ፕሮግራማቸው በምንም ዐይነት ሳይንሳዊና ፍልስፍናዊ መሰረት የለውም።

እንደዚህ ዐይነቱን ውንጀላ ስሰነዝር ፣ አንዳንዶቹ ወይም ደግሞ አብዛኛዎች ማለት ይቻላል ፣ ይህ ደግሞ ከየት የመጣ ዘላባጅ ነው እንደዚህ ዐይነቱን ጥያቄ የሚያነሳ ፤ መሬዎቻቻችንና ፓርቲያችንን በምን ችሎታውና ድፍረት ነው እጋፈጣለሁ ብሎ የተነሳው ብለው ቡራ-ከረዩ ማለታቸው አይቀርም። ይህ ደግሞ የሚገርም አይደለም። ትችታዊ አመለካከት ባልዳበረብት አገርና ፣ በተለይም ደግሞ ሰዎች ከውስጣዊ ይዘትና

ትንታኔ ይልቅ በሚያብለጨልጨና ሰውን በሚያሳስቱ ነገሮች ላይ በቀላሉ በሚማረኩ ህብረተሰብ ውስጥ ረጋ ብሎና ጠለቅ ብሎ ለመወያየት በፍጹም አይቻልም። በዚህም ምክንያት ጥቂት አለሁ አለሁ የሚሉ ሰዎች ብቻ የመናገርና የመወሰን መብት እየተሰጣቸው የብዙ ሚሊዮን ህዝቦች ዕድል ተንጠልጥሎ በመቅረት የድህነቱ ዘመን እየተራዘመ እንዲሄድ ይገደዳል። በአገራችንም ሆነ በውጭ አገር ባለው ኢትዮጵያዊ ዘንድ መወያየት ፣ ጥያቄ ማቅረብና ተከራክሮ አማራጭ መፍትሄ ወይም የትግል ስትራቴጂ ማቅረብ እንደ ወንጀል ይቆጠራል። ይህንም በራሴ ላይ በደረሰው ማረጋገጥ እችላለሁ።

የቅንጅት መሪዎች ከተፈቱ ከጥቂት ወራት ገደማ በኋላ ጥቂቶቹ ወደ አሜሪካ ሲሄዱ ፣ የተወሰኑት ደግሞ ወደ አውሮፓ በመምጣትና በመዘዋወር የአውሮፓን አንድነት ባለስልጣናት ከጎበኙና ስለ ኢትዮጵያ ፖለቲካ ካስረዱ በኋላ በርሊን የሚኖረውን ኢትዮጵያዊ ለማነጋገርና ሃሳባቸውን ለማስረዳት ይመጣሉ። ሶስት ተናጋሪዎች ነበሩ። ስለዲሞክራሲ ደብዛው መጥፋት ፣ ስለጭቆናና ስለ ሊበራል ዲሞክራሲ ያስረዱናል። ሶስቱም ገለጻቸውን ከጨረሱ በኋላ አዳማጮች ጥያቄ እንዲያቀርቡና አስተያየት እንዲሰጡ ዕድል ይስጣቸዋል። ሶስት ተናጋሪዎች አስተያየታቸውን ከሰጡ በኋላ እጄን አውጥቼ ሰፋ ያለ ትንተና አደርጋለሁ። አንደኛ ፣ የግንቦት የህዝብ ድል ለምን እንደከሸፈ ካስረዳሁ በኋላ ፣ በሁለተኛ ደረጃ ፣ የቅንጅት መሪዎች ስለ ምዕራቡ ዓለም ፖለቲካ ያላቸው አስተሳሰብ የዋህነትን ያዘለ ነው ብዬ መታሰብና መጠናት እንዳለበት አሳስቤ ተቀመጥሁ። አንድኛው መሪ ፣ በተለይም በአሜሪካ ላይ ሙሉ ዕምነት እንዳለው ሲያስረዳኝና ኢህአዴግም የውክልና ጦርነት አይደለም የሚያካሂደው እያለ ለማስተባበል ከሞከረ በኋላ ፣ ሁለተኛው ተጋባዥ ደግሞ የዋህ ተባልን እያለ የተናገርኩትን እንደስድብ በመቁጠር ለማስተባበል ሞከረ። ስብሰባውን ያዘጋጀው ፣ እኔ የተናገርኩትን ቀድቶት ስለነበር ማታውኑ በፓልቶክ ውስጥ ዶክተር እከሌ የቅንጅትን መሪዎች ተጋፈጣቸው ብሎ ለአዳማጩ በማሰማት ያጋልጠኛል። ወደ ሌሎች ዝርዝር ጉዳዮች ውስጥ ሳልገባ ፣ አብዛዎቻችን ስለ ፖለቲካ ትግልና ስለ አገር ጉዳይ ያለን አስተያየት ምን ያህል የተጣመመና መሪ ነኝ ያለና የሚል ሁሉ መጠየቅ እንደሌለበት ፣ ሃሳቡ ለክርክር የማይቀርብና መደፈር እንዴለበት አምነን የተቀበልን ብዙዎቻችን ነን። ይህ ዐይነቱ አስተሳሰብ „ንጉስ አይከሰስ ሰማይ አይታረስ“ የሚባለውን የፊዩዳሉን ዘመን አገዛዝ የውሸት ፕሮፖጋንዳና ጭንቅላት አደንዛዥ አባባል ያስታውሰኛል።

በኛ በኢትዮጵያውያኖች ጭንቅላት ውስጥ መቋጠር ያለበት መሰረተ-ሃሳብ ፣ አንድ ሰው የሌላ ሰው አሽከርም ጌታም አይደለም። ማንም ግለሰብ በእግዚአብሄር አምሳል የተፈጠረ በመሆኑ በዚህች ምድር ላይ እኩል ነው። ይሁንና እያንዳንዱ ግለሰብ ደግሞ የየራሱ ተሰጥኦና ችሎታ አለው። ስለዚህም በአንድ ህብረተሰብ ውስጥ እንደሚኖረው ቦታ የየራሱ ህብረተሰብአዊ ደርሻ አለው። በዚህም ህብረተሰብአዊ አስተዋፅዎ ብቻ ሳይሆን እንደማንኛውም ሰው ሙሉ ክብር ይኖረዋል። ሁለተኛ ፣ በማንኛውም ህብረተሰብ ውስጥ ህብረተሰብአዊ መሰላል(Social hierarchy) አለ። ሰለሆነም እያንዳንዱ ግለሰብ ባለው ህብረተሰብአዊ ቦታ ክብር ይሰጠዋል። ስልጣኑን ተጠቅሞ ግን የፈለገውን የማድረግ መብት የለውም። የህዝብ አገልጋይ እንደመሆኑ መጠን የሚሰራቸው ህብረተሰብአዊ ስራዎች ሁሉ ከህገ-መንግስቱ ጋር የሚጣጣሙና የተወሰነ ሎጂክን የተከተሉ መሆን አለባቸው። ተጠያቂ ነው ማለት ነው። በሌላ አነጋገር ፣ የፓርቲ መሪም ሆነ አንድ ባለስልጣን የሞራል ብቃት ያለው ብቻ ሳይሆን ሆደ ሰፊም ለመሆን ችሎታ ያለው መሆን አለበት። ድርጊቱ ሁሉ ቂም በቀልን የሚያስቀድም መሆን የለበትም። ይህ ብቻ ሲሆን አንድን አገር መምራት ይችላል።

ሌላው የኛ ኢትዮጵያውያኖች ችግር ፣ ፖለቲካ ሞራልና ከፍተኛ ስነ-ምግባርን ያካተተና መሰረት ያደረገ መሆኑን ለመገንዘብ ያለን ኃይል በጣም ዝቅተኛ ነው። ከሶስት ሺህ ዐመት ጀምሮ የተካሄደውን የፍልስፍናና የፖለቲካ ትግልን ላጠና ፣ ሞራልን መሰረት ያላደረገ ፖለቲካ የመጨረሻ መጨረሻ ውድቀትን እንደሚያስከትል ነው። ስለዚህም ነው የግሪክ ፈለሳፎች ፣ በተለይም ደግሞ ፕላቶ በፍልስፍናና በፖለቲካ መሀከል ውስጣዊ ግኑኝነት መኖሩን ሲያረጋግጥ ፣ የፖለቲካ ስልጣን በፈላስፎች እስካልተያዘ ድረስ ወይም ደግሞ ንጉሶች ወደ ፈላስፋነት እስካልተለወጡ ድረስ የአንድ አገር ህዝብ ልክ እንደ ዩኒቨርስ ውስጣዊ ስምምነት የሚኖረውን ቆንጆ ህብረተሰብ ለመመስረት ይሳነዋል ብሎ የደመደመው። ምክንያቱም ፖለቲካ መሸወጃ መሳሪያ ወይም አንዱን እያቀረቡ ሌላውን እያራቁ ዕድሜ ማራዘሚያ መሳሪያ ሳይሆን ፣ ለስልጣን እንታገላለን የሚሉ ሰዎች ከፍተኛ የጭንቅላት ነፃነት የሚሰማቸውና ለማድመጥና ትችትን ለመቀበል የሚችሉ ሲሆኑ አገራቸውንም ወደ ገነትነት ለመለወጥ የሚችሉ ይሆናሉ ማለት ነው። ይህንን ማሟላት የማይችሉ ስለ ፖለቲካና ስለ ነፃነት በፍጹም ሊያወሩ አይችሉም።

የሞራልና የስነ-ምግባር እጦት ደግሞ የግዴታ ሀቀኝነትና ኃላፊነት የተሞላበት ትግል እንዳይካሄድ ያግዳል። ግለሰቦችም ሆነ ድርጅቶች በትግል ሂደት የሰሩትን ስህተትም ሆነ ትክክለኛ ስራ ለመገምገምና ፣ ትክክለኛውን ከስህተተኛው ነጥለው በማውጣት ስህተት እንዳይደገም ቆራጥና ትክክለኛ እርምጃ ለመውሰድ ይሳናቸዋል። የሞራልና የስነ-ምግባር እጦትም የግዴታ ውሸትን ያስከትላል። ታጋይ ነን ባዮች ፣ እነሱ የሰሩትን ስህተት በመሸፈንና ራሳቸውን በማወደስ ፣ በሌላ ወገን ደግሞ ሌላውን ወንጀለኛ በማድረግ እነሱ ስልጣን በሚይዙበት ቀን ተመሳሳይ ስህተት ወይም የባሰ ወንጀል በመስራት ሌላና የተመሰቃቀለ ህብረተሰብአዊ ትርምስ ይፈጥራሉ። በዚህም ምክንያት ፣ ባለፉት ሰላሳ ዐመታት የፖለቲካ ትግል ውስጥ ተሳተፍን ያሉ ግለሰቦችም ሆነ ድርጅቶች በተለያየ ደረጃ በአገራችን ላይ ስህተትም ሆነ ወንጀል ፈጽመዋል። ለአገራችን ውድቀትና ውርደት እንዲሁም ደግሞ ብሄራዊ-ነፃነት መከስከስ ተጠያቂዎች ናቸው። ይሁንና ግን ፣ አንዳችም ቦታ ላይ ቆም ብለው ራሳቸውን በመጠየቅና በመጸጸት ህዝባችንን ይቅርታ ጠይቀው አያወቁም። ድሮ የሰራነው ስራ ትክክል ነው በማለት አሁንም ቢሆን ተመሳሳይ ስህተት ሲሰሩና በዚህም በዚያም ብለው የሰውን ኃይል ሲበታትኑ ይታያል። የህዝባችንን የስልጣኔ ጥም እያራዘሙት ነው ማለት ነው።

እንደሚታወቀው ፖለቲካ ትልቅ ኃላፊነትን የሚጠይቅ ነው። የብዙ ሚሊዮን ህዝብን ዕድል መወሰኛ መሳሪያ ነው። የአንድን ህብረተሰብ ታሪክ መስራትና አለመስራት መቻል የሚወሰንበት ልዩ መሳሪያ ነው። የአንድ ህብረተሰብ በስምምነት መኖርና አለመኖር ፣ ወይም ደግሞ ተዝረክርኮ መኖር ወይም አለመኖር በአንድ የፖለቲካ ስልት ሂደት ሊደነገግ ይችላል ማለት ነው። ስለዚህም አንድ ህብረተሰብ ጠንካራና አገር አቀፍ ብሄራዊ ኢኮኖሚ ሊገነባና ብሄራዊ ነፃነቱንም ሊያስከብርም የሚችለው ከቀድሞወኑ ጥበባዊ ፖለቲካ በጭንቅላት ውስጥ ሲቋጠርና እንደመመሪያ ሲወሰድ ብቻ ነው። በመሆኑም ፖለቲካ ሁሉንም ነገር ያካተተና ከዚያ በመነሳት በየደረጃው ህዝባዊ ህልሞች ተግባራዊ መሳሪያ የሚሆኑበት ልዩ ህብረተሰብአዊ ድርጊት ነው ማለት ነው። ባጭሩ ፣ ማንም እየተነሳ ፖለቲከኛ ነኝ በማለት ህብረተብአዊ ትርምስ የሚፈጥርበት ፣ የተንኮለኞችና የስልጣን ጥመኞች መሳሪያ አይደለም። አርቆ አስተዋይነትን ፣ ጠለቅና ሰፋ ያለ ዕውቀትን ፣ ግን ደግሞ በግልጽ መነጋገርንና ለአገር የሚበጅ አመለካከትን ለመሰንዘር የሚጠይቅ ግዙፍ ጽንሰ-ሃሳብ ነው።

ስለዚህም ለህዝብ ነጻነት እንታገላለን የሚሉ ሰዎች ፣ አንደኛ ፣ ከስሜታዊነት መራቅ አለባቸው። ሁለተኛ ፣ በራሳቸው የሚተማመኑና የማይደነግጡ መሆን አለባቸው። ሶስተኛ ፣ ሆደ ሰፊ መሆን አለባቸው። አራተኛ ፣ በፕርንሲፐልስ የሚመሩ መሆን አለባቸው። አምስተኛ ፣ የራሳቸውን ጥቅም ከአገራቸው ጥቅም በፊት ማስቀድም የለባቸውም። ስድስተኛ ፣ ማንኛውንም አገር የሚመለከት ጉዳይ ከመወሰናቸው በፊት መመካከርና ከህገ-መንግሰቱ ጋር የሚጣጣም መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው። ተግባራዊ የሚሆኑ ውሳኔዎች አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ ጎን እንደሚኖራቸውና እያንዳንዱን ዜጋ እንደየቦታው እንደሚነካ ማውጣትና ማውረድ አለባቸው። ሰባተኛ ፣ ዞሮ ዞሮ ሞራል ፣ ስነ-ምግባርና አርቆ ስተዋይነት የአንድ ፖለቲካ ሂደት መመዘኛዎች ናቸው።

## የህብረተሰብን አወቃቀር ህግ የመረዳት ችግር !

*“ All errors in politics and ethics have sprung … from false ideas which are closely connected with errors in physics and ignorance of the laws of nature.”(Seneca)*

ማንኛውም የፖለቲካ ሂደት ስህተት የሚከሰተው የተፈጥሮን ህግ መረዳት ካለመቻል ብቻ ሳይሆን ማንኛውም ህብረተሰብ የራሱ የሆኑ ከትውልድ ወደ ትውልድ በሚተላለፉ ኖርሞችና ባህሎች እንደሚገዛ ለመገንዘብ ካለመቻል ነው።

በአውሮፓው ህብረተሰብ ታረክ ውስጥ ፈላስፋዎች ሆን ብለው ራሳቸውን ያሰጨንቁ የነበረው የተፈጥሮን ህግ መረዳት ብቻ ሳይሆን የሰዎችንም ባህርይና ድርጊት መመርመርና አጥፊዎች ከሆኑ ደግሞ እንዲታነጹ ማድረግ ነው። በግሪክ ፈላስፋዎች መሰረት ወደዚህች ዓለም ላይ ስንወረወር ጥሬ አስተሳሰብ ኖሮን ነው የምንፈጠረው። በዕድገታችን ሂደት ውስጥ በምናገኛቸው እንክብካቤዎችና ዕውቀቶች እንደ ዕውቀቱ ዐይነት ባህርያችንና ድርጊታችን ይቀረጻሉ። ማንኛውም ሰው ስሜታዊነት(emotion) ፣ ጥልቅ ስሜታዊነት ወይም ንዴትና(passion) አርቆ-አስተዋይነት (reason or rationality) በጭንቅላት ውስጥ አሉ። አርቆ አስተዋይነት በአሸናፊነት ሊወጣ የሚችለው አንድ ሰው በሰፊውና በጥልቀት እያወቀ

ሲሄድና ምሁራዊነትን ከሰብአዊነት ጋር ማጠመር የቻለ እንደሆን ብቻ ነው። ይሁንና ይህም ሆኖ አርቆ አስተዋይነትንና ሎጂክን የአገዛዝ መመሪያ አድርገው የሚጠቀሙ ጥቂቶች ብቻ ናቸው። በህብረተሰብ ታሪክ ውስጥ እንደታየውና በየጊዜው በሚከሰቱ የኃይሎች አሰላለፍ መለዋወጥ በአሸናፊነት የሚወጡ የራሳቸውን ርዕይ በመንግስት መኪና ላይ በማሰፈርና ተቀባይነት እንዲኖረው በማድረግ ህብረተሰብአዊ ኖርም እንዲኖረው ያደርጋሉ። በተለይም የዜና ማሰራጫዎችን በመቆጣጠር ሰፊው ህዝብ ውሸትን ከዕውነት እንዳይለይ ያደርጋሉ። ስለዚህም ፣ አርቆ ማሰብ የሚለው አነጋገር በአውሮፓው የህብረተሰብ ታሪክ ውስጥ እነ ፕላቶን ካዳበሩት መሰረተ-ሃሳብ በመውጣት ልዩ ዐይነት የራስን ጥቅም ማሳደጃ መሳሪያ ሆኗል። የግለሰቦች ሚናና (Methodological Individualism)የራስን ጥቅም ማሳደድ (Utilitarian Thinking) ተቀባይነት እያገኙና የበላይነትን እየተቀዳጁ በመምጣታቸው ማንኛውም ፖሊሲዎች ከዚህ ግለሰብአዊነትን ከሚያጠንክር አኳያ ስለሚነደፉና ተግባራዊ ስለሚሆኑ ህብረተሰበአዊ ቅራኔዎች እንዲከሰቱና ግጭቶች እንዲፈጠሩ መንገድ እየከፈቱ ነው። ከዚህ ባሻገር ፣ ስለምዕራቡ አርቆ-አሳቢነት በሚነሳበት ጊዜ የሚቀርበው ጥያቄ በቴክኖሎጂ በከፍተኛ ደረጃ መጥቆ የሄደው ዓለም ፣ ዓለምን ለማጥፋት የሚያስችሉት የአቶሚክ ፣ የባዮሎጂካልና የኬሚካል መሳሪያዎች አምርቶና አከማችቶ ጊዜን የሚጠባበቅ ይመስላል። ስለዚህም ከድግሱ በፊት... እንዲሉ በአሸባሪ ኃይሎች ስም እያሳበበ ከአፍጋኒስታን እስከፓኪስታንና እስከ ሱማሊያ ድረስ በየዋህ ህዝቦች ላይ የተወሳሰበ የጦር መሳሪያውን እየተለማመደ ነው። ይህ ዐይነቱ ጦርነትና የዓለምን አካባቢዎች አየር የሚበርዙና ወደፊትም ለድርቀትና ለምግብ እጥረት የሚሆን የአስተራረስ ዘዴና የጂን ቴክኖሎጂ ማስፋፋት የምዕራቡ ዓለም ሁሉን ነገር ከገንዘብና ከትርፍ አንፃር ብቻ የሚያሰላና ዓለምንም ለረጅም ዐመታት ተቆጣጥሮ ለመኖር እንደሚፈልግ ነው። ፖለቲካውም በምንም ዐይነት በዕውነተኛው የአርቆ አስተዋይነት ፖለቲካና ሎጂክ የሚደገፍ አይደለም። ስለሆነም ፣ የሰለጠነው የምዕራቡ ዓለም የእነ ፕላቶንና ፣ ከ14ኛው ክፍለ-ዘመን ጀምሮ ደግሞ እንደገና ያንሰራራውን የሰብአዊነትንና የአርቆ-አሳቢነትን መርህ በመከተል ሳይሆን ፣ ፖሊሲዎቹ ሁሉ ከጥቅም አንፃርና ከጂኦ-ፖለቲካ አኳያ በመተለም የዐለም ህዝቦች ተስማምተው በመኖር ሰላምና ብልጽግናን እንዳይጎናጸፉ የሚያደርግ የተፈጥሮን ህግ የሚጥስ ነው። በመሆኑም ፣ ስለ-አርቆ-አሳቢነት በሚወራበት ጊዜ የዕንሰ-ሃሳቡን ዕድገት ክህብረተሰብ ዕድገትና ከኃይል አሰላለፍ ለውጥ ጋር እያገናኙ ለመተንተንና ለመረዳት መቻል ያስፈልጋል።

ወደ አገራችን ስንመጣ እንደ ምዕራቡ ስልጣኔ ፣ ለጭንቅላት መዳበርና ራስን ለመቆጣጠር የሚያስፈልጉ እንደ ሜታፊዚክስ ፣ አርቆ-አሳቢነትና (rationalism) ሎጂክ አስፈላጊና መሰረታዊ የትምህርት ዘርፎች ሆነው ባለመሰጠታቸው ንጹህ የአካዳሚ ዕውቀት ብቻውን ወደ ፊት ሊያራምደን አልቻለም። ከ1950ዎቹ ዐመታት ጀምሮ ብቅ ያለውና በአካዳሚ ዕውቀት ብቻ የተካነው ምሁር የዕድገት አጋዥና ስልጣኔ አፍላቂ መሆኑ ቀርቶ እንዲያውም ተቀናቃኝ ሆነ። በዘመናዊነት ስም የገባው ቴክኖሎጂ ዕድገት አጋዥ ያልሆነ ፣ የፍጆታ አጠቃቀምና የአመራረት ዘዴ ህብረተሰብአዊ ዝብርቅርቅነትን አስከተለ። ይህ ሁኔታ ለአመጽና አርቆ ላለማስብ መሰረት ጣለ።

ከዚህ አጭር ትንተና ስንነሳ የእኛ ዕወቀት ሁኔታና የጭንቅላታችን በዚህ ሆነ በዚያኛው አርቆ-አስተዋይነት ክልል ውስጥ ብቻ መሽከርከር ፣ ሚናችን ውስንና ደርጊታችንም ሁለንታዊ መሆኑ ቀርቶ በክስተት ላይ ብቻ የተመሰረተ እንዲሆን አድርጎታል። ስለሆነም ፣ የኛ ሚና ከጊዜና ከነባራዊ ሁኔታ ውጭና እንዲሁም ደግሞ ከቀሰምነው ዕውቀት ባሻገር ሊሆን አይችልም። እንደ አስተዳደጋችንና አካባቢያችን እንዲሁም ደግሞ ዕውቀታችን ጥልቀት ፣ አስተሳሰባችን ወይ ጠባብ ካሊያም ደግሞ ሰፋ ያለ ይሆናል። ስለሆነም አመጣጣችንን መካድና አለመካድ ፣ የህበረተሰብአችንን አኗኗር በቅጡ መገንዘብና አለመገንዘብ ፣ ይህንንም መሰረት አድርጎ ለመለወጥና አለመለወጥ መቻል የሚወሰነው በቀሰምነው ዕወቀትና እንደመመሪያ በወሰድነው ርዕይ ነው። እንደገና ፣ በሶክራተስና በፕላቶን በአንድ በኩል ፣ በሌላ ወገን ደግሞ በሶፊሰቶች መሀከል የተካሄደው ትግልና እስከ መጨረሻው ማእከለኛው ዘመን ድረስ የዘለቀው ትግልና ተፈጥሮንና የሰውን ልጅ ሚና መገምገሙና ዛሬም ያለው ያልተቋረጠ ትግል የሚያረጋግጠው *ታሪክ የመጨረሻዋን ፍርድ እንዳልሰጠች ነው።* ዛሬ ዓለምን አንድ ወጥ ለማድረግ የሚደረገው አደገኛ ሙከራ የሚያመለክተው ለጊዜውም ቢሆን የሶፊስቶችና የኢምፔሪሲስቶች አስተሳሰብ በአሸናፊነት በመውጣቱ ነው። የምዕራቡ ዓለም ግሎባላይዜሽን ሲል እኛም አብረን እንላለን። የነጻ ገበያ ሲል እኛም እናስተጋባለን። የምዕራቡ ዓለም አሸባሪዎችን መዋጋት አለብን ሲል እኛም የሞት የሽረት እያልን እንጮሃለን። ከዓለም ባንክና ከዓለም አቀፍ የገንዘብ ምክርና ድጋፍ ውጭ ኢኮኖሚያችንን መገንባት የማንችል መሆናችንን ከተቀበልን ዐመታት አልፎናል። በዚህም ሴናካ እንዳለው የተፈጥሮን ህግንና የሰውን ልጅ የማሰብ

ኃይል ቁጥር ውስጥ ባለማስገባት የተፈጥሮን ህግጋት እየጣስን ነው። በመሆኑም ፖለቲካችንና ድርጊታችን ሁሉ ከዚህ ኢምፔሪሲስታዊ ወይም ፖዘቲቭ ሳይንስ የፈለቀ ነው ብል ስህተት አይደለም። በሌላ አነጋገር ፣ በስልጣኔና በህብረተሰብ ታሪክ ውስጥ እንዲሁም ደግሞ የሰውን ልጅ ታሪክ ሰሪነት ለማረጋገጥ የተደረገውን እልክ አስጨራሽ ትግል ከቁጥር ውስጥ ባለማስገባትና በተወሰኑ ነገሮች ላይ ብቻ በመጠመድ ወደ ሚያረጋጋና ኃይል ወደ ሚያሰባስብ ሁኔታ ከማምራት ይልቅ ለመጠፋፋት ቅድሚያ እንሰጣለን። ሃሳባችንና አመለካከታችንን ትችታዊ(Critical) በሆነ መልክ ከማዳበር ይልቅ የኔ ብቻ ነው ትክክል በማለት ቡድናዊ ስሜት እንዲዳብር መንገድ እንከፍታለን። ባጭሩ ፣ ሰብአዊነትን ከማስቀደም ይልቅ ፣ ጎሰኛነትንና ጎጠኝነትን እያስቀደምን ለጥፋታችን ሁኔታዎችን እያመቻቸን ነው።

በመሆኑም ፣ የኢትዮጵያን ሁኔታና የፖለቲካ አወቃቀር በዲያሌክቲካል መነጽር ከታሪክና ከህብረተሰብ ሂደት ጋር በማነፀፃር መገምገምና ማስተማር ካቆምን ዘመናት አልፈዋል። አቀራረባችንና አተናተናችን ታሪክን ወደ ማያሰራ ሁኔታ እንድናመራ እያደረገን ነው። ስለዚህም የህብረተሰብአችንን ውስጣዊ ህግ ለመረዳት አስቸጋሪ ሁኔታ እየተፈጠረ ነው።

አንድ ህብረተሰብ የራሱ ህግጋት አለው ስንል ምን ማለታችን ነው? በሰው ልጅና በተፈጥሮ መሀከል ያለው ግኑኝነት የአንድን ህብረተሰብ ዕድገት ይወስናል ስንል ምን ማለታችን ነው? የሰዎች የማሰብ ኃይልም በህብረተሰብ ዕድገትና በተፈጥሮ ላይ አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ተጽእኖ ይኖረዋል ስንል ምን ማለታችን ነው? በጣም አስቸጋሪ ጥያቄና የብዙ ገጾች መልስ የሚያስፈልገው ነው። የአንድ ህብረተሰብ ዕድገትና ደረጃን ጠብቆ ልክ እንደ ተፈጥሮ ከታች ወደ ላይ ማደግ(Process Metaphysics) የሚወሰነው ፣ የአንድ ህብረተሰብ የማሰብ ኃይልና የዕውቀት ደረጃ ሲታወቅ ብቻ ነው። የየግለሰቦች አስተሳሰብና ችግርን የመፍታት ሁኔታ ደግሞ ሊወሰን የሚችለው ግለሰቦች ከትውልድ ወደ ትውልድ በተሸጋገረ ባህልና ኖርምስ መጠመዳቸውና አለመጠመዳቸው የታወቀ እንደሆን ብቻ ነው። ግለሰብአዊ ድርጊትና ተፈጥሮን እየቃኙ እሱን መኮረጅ ሊወሰን የሚችለው የተወሰነ ዕወቀት ሲነጠፍና የማያቋርጥ ምርምር ማድረግ ሲቻል ብቻ ነው። ባጭሩ ፣ የህብረተሰብ ህግ ስንል በሰዎች መሀከል የሚኖረው ግኑኝነት ፣ ሰዎች ራሳቸውን ለማሸነፍ ሲሉ የሚያካሂዱት ምርታዊ ክንውን ፣ የአመራረታቸውን ስልት ለማሻሻልም ሆነ ለማሻሻል አለመቻል ፣ ጠቅላላው የኑሮአቸውን ሁኔታ ለማሻሻልና በተቀነባበረ መልክ ለማዘጋጀት መቻል አለመቻል ፣ ተዝረክርኮ መኖር አለመኖር ፣ እንደ ህብረተሰብ ህግ ሊወሰዱ ይችላሉ። ከዚህም ስንነሳ ፣ የአመራረትንና የምርት ዐይነት ሁኔታ ሊወሰን የሚችለው የምርት ግኑኝነት ምን ይመስላል? ውስጣዊ ህጉስ ምንድ ነው? ብለን ስንጠይቅና ስንረዳ በእርግጥም አንድ ህብረተሰብ በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝና ያሉትን ችግሮች በአዲስ ስትራቴጂ ለመወጣት የሚችልና የማይችል መሆኑን ልንረዳ እንችላለን። በተጨማሪም ፣ ስለ ስራ ክፍፍል መኖርና መዳበር ወይም ደግሞ ውስንነት ፣ በተለያዩ የኢኮኖሚ መስኮች ዘንድ ስለሚኖረው ውሰጣዊ ግኑኝነት ፣ከሌለስ ለምን ሊኖር እንዳልቻለ ፣ ስለፍጆታ(commodity)ምርት መዳበርና በገንዘብ መለወጥ ፣ስለ ገንዘብ የተለያየ የዕድገት ደረጃ ፣(metamorphoses) በገንዘብና በሌላው የኢኮኖሚ ዘርፍ ስለሚኖረው ግኑኝነት ፣ ከሌለስ ምክንያቱ ምድን ነው ፣ ስለገንዘብ በፍጥነት መሸከርከር(velocity of money) አለመሸከርከር ፣ እነዚህ ሁሉ መሰረተ-ሃሳቦች አንድ ህብረተሰብ በየትኛው የዕድገት ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ይነግረናል። ከዚህም በመነሳት ፣ በጠቅላላው ህብረተሰብ ውስጥ ስለሚኖረው ውስጣዊ ግኑኝነት(organic link) ፣ ስለባህል መዳበርና አለመዳበር ፣ባጭሩ የህብረተሰቡ አመለካከትና እራሱን ለመለወጥ ዝግጁ መሆንና አለመሆን ፣ ስልጣንን የጨበጠው መደብ ባህርይ ፣ የምርት ኃይሎችን ፣(production forces) ሁኔታ ፣ ከተማዎችን ለመቆርቆርና ለማስፋፋት ያለው ችሎታና ፍላጎት ፣ ወይም ደግሞ ያለመቻል እንደ አንድ ህብረተሰብ ህግ ሊቆጠሩ ይችላሉ። ምክንያቱም ፣ አንድ ህብረተሰብ ከታች ወደ ላይ እያደገ መሄድና በተለያዩ መሳሪያዎች መተሳሰር ስላለበትና የዕድገቱም መለያ ራሱን ከማንኛውም አደጋ ለመከላከል ያለው ችሎታ በዕደገቱ ደረጃ ስለሚወሰን መሰረታዊ ነገሮች ከጎደሉና እዚያው በዚያው ብቻ የሚንቀሳቀስ ከሆነ ፣ ይህ ዐይነቱ ህብረተሰብ ወደ ኋላ በሚጎትትና ዕደገትን አንቆ በያዘ ውስጣዊ ኃይል ይገዛል ወይም ደግሞ ዕደሉ ይወሰናል ማለት ነው።

ከዚህ አነስተኛ ትንተና ስንነሳ ፣ እያንዳንዱ ህብረተሰብ የየራሱ ጉዞና የዕድገቱንም ደረጃ የሚወስኑት ነገሮች አሉ ማለት ነው። በዚህም ምክንያት ነው በተለያዩ አገሮች የተለያዩ የአመራረትና የአስተራረስ ስልትና አስተሳሰቦች የነገሱት። በአንድ በኩል ይህ ልዩነት(variation) ጥሩ የሆነውን ያህል ፣ በሌላ ወገን ግን ማንኛውም ህብረተሰብ

ለህይወቱ የሚያስፈልጉትን ማንኛውም ነገር ማሟላት መቻል አለበት። መብላት ፣ መጠጣት ፣ መጠለያና ልብስ ማግኘት ዓለም አቀፋዊ ኖርምስ ወይም ደግሞ መሟላት ያለባቸው መሰረተ-ሃሳቦች ናቸው ማለት ነው። በተጨማሪም ፣ ማንኛውም ህዝብ ስሜት አለው። ቅሬታውን ጮህ ብሎ ማሰማት ይፈልጋል። ጭንቅላቱ ውስጥ የሚብሰለሰለውን ውጭ አውጥቶ መናገር ሲችል ልዩ ስሜት ይሰማዋል። ሰውነቱ መፍታታት ይጀምራል። እነዚህ ዩኒቨርሳል ህጎች ናቸው። የሰውን ስሜት ማፈን ማለት ዕድገት እንዳይኖር እንቅፋት መፍጠር ማለት ነው። እንደዚህ ዐይነቱ ስሜትን የማዳበር ፣ ሃሳብን ወደ ውጭ አውጥቶ እንዲናገሩና ተቀባይነት እንዲኖረው ማድረግ የባህል ዕድገት ነፀብራቆች ናቸው። ከላይ ወደታች በሚወረወር አዋጅ የሚከናወን ወይም ደግሞ ይህንን ርዕዮተ-ዓለም እንቀበላለን ስለተባለና ጥቂቶች ተነስተው ስለ ደሰኮሩ ተግባራዊ የሚሆን አይደለም። ይህ ቢሆን ኑሮ የደርግ ዘመን የአስራሰባት ዐመት ሶሻሊዝም የኢትዮጵያን ህዝብ አስተሳሰብና ድርጊቱን መለወጥ በቻለ ነበር።

እዚህ ላይ አንድ ድሮ በተማሪው እንቅስቃሴ ውስጥ የተካፈለና ጀርመን አገር ብዙ ዐመታት የኖረ አሁን አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ የሚያስተምር ወደዚሁ ጀርመን በቅርብ መጥቶ ያጫወተኝን ልንገራችሁ። ሰውዬው ከሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል የመጣና አዲስ አበባ ያደገ ነው። የተወለደበትን አካባቢና የሰውን አስተሳሰብ እምብዛም የሚያውቅ አይደለም ። በኮሙኒሰት ርዕዮተ-ዓለም ሰው እንደሚለወጥ በጊዜው ዕምነት እንደነበረውና አሁን ግን የተወለደበትን አካባቢ ደጋግሞ ከጎበኘ በኋላ የሰው አስተሳሰብ ከድሮው ሁኔታው ምንም እንዳልተቀየረ ይገነዘባል። በቀላሉ የማይታዘዝና አመጸኛነት እንደሚያጠቃው ይመለከታል ። በአንዳንድ ቦታዎችም አሁንም ሽፍታዎች እንዳሉና ይህም የኑሮአቸው መሰረት እንደሆነ ለመገንዘብ ችሏል። ስለዚህም ፣ ድሮ ዝም ተብሎ ሶሻሊዝም ሲለፈፍ እንደነበርና ትግሉ መላ እንዳልነበረውና በመሰረቱ የሰዎች አስተሳሰብና የአኗኗር ስልት እንዳልተቀየረ ይገነዘባል። ይህም የሚያመለክትው ፣ እንደኛ ያለውን ህብረተሰብ አስተሳሰብ ለመለወጥና የስልጣኔ ባለቤት ለማድረግ የሚቻለው ከላይ ወደ ታች በሚወረወር እንደ ሶሻሊዝም መሰል መፈክር ወይም ደግሞ ዛሬ እንደሚታየው በገበያ ኢኮኖሚ ፍልስፍና ሳይሆን ፣ እነ ሺለርና ዊልሄልም ሁምቦልድት ያዳባሩትን ጭንቅላትን ፈታ የሚያደርግና አስታሰስብን ብሩህ የሚያደርግ ሁለ-ገብ ትምህርት ሲዘረጋ ብቻ ነው። በአውሮፓ ውስጥ ፣ ታሪክ የተሰራው በዚህ መልክ ብቻ እንጂ በመጀመሪያ የሰዎችን አስተሳሰብ በፍጆታ አጠቃቀም ዙሪያ እንዲሽከረከር በማድረግ ወይም በሶሻሊዝም ፕሮፓጋንዳ አንዱን የህብረተሰብ ክፍል በሌላው ላይ በማስነሳት አይደለም።

ይህ ማለት ምን ማለት ነው? የህብረተሰብአችንን ህግና የተፈጥሮን ሁኔታ ሳናጠና በአዋቂ-ነን ባይነትና በግብዝነት ተግባራዊ የምናደርጋቸው ፖሊሲዎች ሁሉ የመጨረሻ መጨረሻ ወደ ጥፋት ያመሩናል። ለዚህም ነው የደርግ ሶሻሊዝም የከሸፈው። ከአስራስምንት ዓመት ጀምሮ በገበያ ኢኮኖሚ ስም የሚካሄደው ፖሊሲ ከድህነትና ከረሃብ ሊያላቅቀን ያልቻለው አገዛዙና አማካሪዎቹ የተፈጥሮንና የህብረተሰብአችንን ህግ ለመረዳት ባለመቻላቸው ወይም ባለመፈለጋቸው ነው። ያውም በዶለር እየተከፈላቸው የሚያማክሩ ኤክስፐርቶች የበላይነትን በተቀዳጁበት ዘመን ፣ በየጊዜው ለሚከሰቱ ችግሮች መፍትሄ ከመሰጠት ይልቅ ራሳቸው ችግር ፈጣሪና ህብረተሰባዊ ምስቅልቅል ለመፍጠር በቅተዋል። ከዚህ ስንነሳ ፣ እኛ ተቃዋሚ የምንባል ፣ በተለይም ደግሞ በፓርቲ ደረጃ የተደራጁ ስማቸው በየጊዜው የሚጠራው ፣ በእርግጥስ የኢትዮጵያን ችግር ለመቅረፍ የሚያስችል ፍቱን መሳሪያና ፖለሲ አላቸው ወይ? ፖሊሲያቸውስ በአንዳች ፍልስፍና ላይ የተመሰረተ ነው ወይ? ካላቸውስ ፖሊሲያቸው ወደ ምን ዐይነት ህብረተሰብ ነው የሚያመራን?

በእኛ ኢትዮጵያኖችም ሆነ በብዙ የአፍሪቃ አገሮች ያለው ቸግር የሃሳብን (Idea) መንሸራሸር እንዲሁም ደግሞ የየራስን አመለካከት ወደ ውጭ ወጣ በማድረግ ተከራክሮ ለህብረተሰብ ዕደገት የሚበጀውን ዕቅድ ለመንደፍ ያለመቻል ነው። በብዙዎቻችን ዘንድ ነገሮች ወይም የተወሰኑ አስተሳሰቦች በአንድ መንፈሳዊ ኃይል እንደተሰጡና እነዚህም መጣሰ እንደሌለባቸው የተቀበልን ይመስላል። የእግዚአብሄርን ህግ የጣስ ገሀነመ-እሳት ይገባል እንደሚባለው አነጋገር ፣ ከተወሰኑ ኖርሞች ዘነፍ የሚል እንደ ኃጢአተኛ ወደ ሚታይበት ደረጃ ከተደረሰ ዘመናት አልፈዋል። በመሆኑም ፣ በአገራችን ውስጥ የተካሄዱት አገርንና ባህልን አፍራሽ ፖሊሲዎች ሁሉ በሃሳብ ዙሪያ እያብጠለጠለን እንድንወያይ ለማድረግ ባለመቻላችንና ከጠራ ሀሳብ የፈለቁ የራሳችን አማራጭ ፖለሲ ስለሌለን ፣ ወይም ደግሞ አለን ብንል እንኳ ፣ በነጻ ገበያ ሎጂክ ውስጥ የሚሽከረከር ስለሆነ ይህ ዐይነቱ ፖሊሲ በመሰረቱ የአገራችን ችግር ሊፈታ የማይችል መሆኑን እያመለከተ ነው። በሌላ ወገን ደግሞ ፣ የነጻ ገበያ ሎጂክ ተቀባይነት ያገኘ ቢመስልም በተለያዩ ርዕዮተ-ዓለም ስም የሚምሉና እሱን ተግባራዊ ለማድረግ ፍላጎት አለን የሚሉ የተለያዩ ድርጀቶችም ሆነ

ፓርቲዎች እንደ አሸን ፈልቀዋል። ከሶሻል ዲሞክራቲክ ፓርቲ እስከ ሊበራል ዲሞክራሲ ፣ እንዲያም ሲል ንጉሳዊ አገዛዝን ለማምጣት የሚታገሉ እዚህና እዚያ ሲንቀሳቀሱ ወይም ድምጻቸውን ሲያሰሙ ይታያሉ። የሚነሳው ጥያቄ ፣ አንደኛ ፣ አገሪቱ እነዚህን ዝብርቅርቅ ፓርቲዎች ሁሉ ለማስተናገድ ትችላለች ወይ? ሁለተኛ ፣ በእርግጥስ እነዚህ የተለያዩ ፓርቲዎች የአገራችንን የተወሳሰበ ችግር የመፍታት ብቃትና ኃይል አላቸው ወይ ? ስልጣን ለመያዝ ብቻ ነው ወይ የሚታገሉት? ለአገራችን አንድነትና ዕድገት እንታገላለን የሚሉ ከሆነ ደግሞ ለምንስ በተለያያ ርዕዮተ-ዓለም ስር ለመሰለፍ ተገደዱ? ይህ ሁኔታ የሃሳብ መበታተንና የኋላ ኋላ ደግሞ ወደ ግጭት አያመራንም ወይ?

በተለያየ የፓርቲ ስም የሚንቀሳቀሱት ድርጅቶች አንድ እስካሁን ያልተገነዘቡት ነገር አለ። በአውሮፓ ታሪክ ውስጥ ብቅ ያሉት ፓርቲዎችና ዛሬ የበላይነትን የተቀዳጁት በአንድ ጊዜ ከሰማይ ዱብ ያሉ አይደሉም። የህብረተሰብ ዕድገትና የኃይል አሰላለፍ ለውጥ ውጤቶች ናቸው። በሃሳብና በርዕይ ደረጃ ሊበራሊዝም በ17ኛው ክፍለ ዘመን የመርካንታሊዝምንና የባላበቶችን የበላይነት እየታገለ የመጣ ቢሆንም ፣ ግለሰቦች በፓርቲ ደረጃ መደራጀት የጀመሩተ በ19ኛው ክፍለ-ዘመን ፣ ወይም ደግሞ በ20ኛው ክፍለ-ዘመን የተቋቋሙ ናቸው። ከኮንሰርቫቲቭና ከሊበራል ፓርቲዎች ቀድሞ የተደራጁት የኮሙኒስት ፓርቲዎች ፣ በኋላ ደግሞ ከዚህ ተፈንግጠው የወጡ የሶሻል ዲሞክራቲክ ፖርቲዎች ናቸው። በህብረተሰብአቸው ታሪክ ውስጥ እነዚህ ሁሉ ፓርቲዎች በየጊዜው የአስተሳሰብን ለውጥ እያሳዩ የመጡ ናቸው። ከሰውነታቸው ጋር የተወሰነ የአሰራር ኖርምን አዳብረዋል። ህግንና ስራን ማክበር ፣ በዲሲፕሊን ለመኑበት ርዕይ መስራት ፣ ወደ ውጭ አውጥቶ መከራከርና ሌላውን ለማሳመን መሞከር ፣ ሰዓትን ማክበርና በሌላ ወገን ደግሞ በግትር ሃሳብ ላይ አለመጽናትና ወደ ጠብ አለማምራት ፣ እንዲሁም በሚያስማሙ ነገሮች ላይ ለመስራት መቻል ፣ እነዚህ ሁሉ ከበርቴያዊ ኖርሞች ናቸው። ቀስ በቀስ ከታች ወደ ላይ ያደጉ ያሰራር ዘዴዎች ናቸው። ከዘመነ ሬናሳንስ ጀምሮ ቀስ በቀስ ስር እየሰደደ የመጣው ሰፋ ያለ ምሁራዊ እንቅስቃሴ ውጤቶች ናቸው። ባጭሩ ፣ በአውሮፓ ታሪክ ውስጥ የፓርቲዎች አነሳስና ዕድገት የኢኮኖሚ ዕድገት ፣ የአዳዲስ ሃሳቦች መፍልቅና የኃይል አሰላለፍ ውጤቶች ናቸው። በመሆኑም ፣ እያንዳንዱ ፓርቲ ቆሜለታለሁ የሚለውን የህብረተሰብ ክፍል ጥቅም የሚያስቀድም እንጂ ጠቅላላውን ህዝብ የሚወክል አይደለም። በሌላ ወገን ግን ፣ የሰላሳ ዐመቱን የምዕራብ አገሮችን ፖለቲካ ታሪክና የፓርቲዎችን የኢኮኖሚና የማህበራዊ ፖሊሲ ለተከታተለ ፣ በርዕይ ደረጃ እየተቀራረቡ መጥተዋል። ከግራ እስከ ቀኝ ፣ ከሊበራሎች እስከ ሶሻል ዴሞክራቶች ድረስ ሁሉም የኒዎ-ሊበራል የኢኮኖሚ ፖሊሲን እንደተቀበሉ ማረጋገጥ ይቻላል። የሚለያዩት ጥቃቅን በሆኑ በቀረጥና በፊናንስ ፖሊሲ መስመሮች ሲሆን ፣ እንዴት አድርገን ሀብት ከታች ወደ ላይ ፣ ወይም ደግሞ ከላይ ወደ ታች እናሸጋሽግ በሚለውና በጣም የተወሳሳቡ የሂሳብ ሞዴሎችን በመፍጠር ነው። እንደዚህ ዐይነቱ ፖለቲካና ፖሊሲ ከትራዲሽናል ሚናቸው እየራቁ እንዲመጡ ሲያስገድዳቸው ፣ የግዴታ በፓርቲዎችና በፋይናንስ እንዲሁም ደግሞ በኢንዱስትሪ ካፒታል መሀከል ያለውን ግኑኝነት እያቀረበው እንደመጣ መመልከት ይቻላል። በዚህም ምክንያት ፣ ብዙ ፓርቲዎች ሎቢስቶች የተሰገሰጉብትና በየሚንስትሪዎችም ውስጥ ህግ አርቃቂ በመሆንና ለህዝብ ተወካዮች በማቅረብ ከሰማንያ በመቶ በሆነው ህዝብ ህይወት ላይ ደንጋጊ ሆነዋል ማለት ይቻላል። ባጭሩ ፣ የትላንትናው የሶሻል ዲሞክራቲክ ፓርቲ የዛሬውን ዐይነት አይደለም። እንዲሁም ሌሎች ፓርቲዎች በፍጹም ተለውጠዋል ማለት ይቻላል። አሁን በደረሰው የፊናንስ ቀውስና የስራ እጦት መጨመር ሚናቸውን እንደገና ለመፈለግና ወደ ቀድሞው ደንበኞቻቸው ጋ ጠጋ ለማለት ወዲያና ወዲህ በማለት ሲራወጡ ይታያል። በዚህ ዐይነት ቅራኔ ወስጥ ነው ብዙ የምዕራብ አውሮፓ ፓርቲዎች የሚገኙት።

ከዚህ አጠር ያለ ትንተና ስንነሳ ፣ በአገራችን ብቅ ያሉት ፓርቲዎች የጠቅላላውን ህዝብ ጥቅም አስጠባቂዎች ናቸው ወይ? ወይስ የተወሰኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን የሚወክሉ ናቸው? በህብረተሰብ ዕድገት ታሪክ ውስጥ ያለፉ ናቸው ወይ? ወይስ ከላይ እንደመና የተወረወሩና ይህንን ብናደረግ ይሻላል ብለው የሚንቀሳቀሱ ናቸው? በርግጥስ በመረጡት ስም ያምኑበታል ወይ? ዲሞክራትስ ናቸው ወይ? ከሆኑስ እንዴት ልንመዝናቸው እንችላለን? ጭንቅላታቸውንና ልባቸውን ከፍተን በማየት ዲሞክራቶች መሆናቸውን ማረጋገጥ የምንችልበት መሳሪያ አለን ወይ? ዛሬ ግራ አሳይተው ነገ ቀኝ ቢሸመጥጡስ? ይህ ግልጽ እስካልሆነ ድረስ አብዛኛዎቻችን የዚህ ወይም የዚያኛው ፓርቲ ደጋፊዎች ነን የምንልና እስከዚህም ድረስ በጭንቅላታችን ውስጥ ያላብጠለጠልን ዝም ብለን ነው የምንጮኸውና የምንለፋው ማለት ነው። ይህ በደንብ ሳይጠናና ውይይት ሳይደረግበት አንድ ርዕዮተ-ዓለም ተቀብያለሁ ብሎ የሚመሰረት ድርጅትና የሚወጣው ፕሮግራም ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ያመዝናል። የድርጀቱ መሪዎችም ሆነ አባላት በርዕይ ዙሪያ ያልተሰበሰቡና በአንዳች ፍልስፍናም የማይመሩ ሰለሚሆን ፣ ፓርቲው ሰፋ ያለ ርዕይን ከማዳበርና ለክርክር በሚያመች መልክ ከመደራጀቱ ይልቅ ከመጀመሪያውኑ ቡድናዊ ስሜት እንዲኖረው

ይደረጋል። በድርጅቱ ውስጥ የግዴታ የፊዩዳል መሰል ሂራርኪ ስለሚፈጠር ሃሳብን ለማንሸራሸርና ችግር ፈቺ እንዲሆን ለማድረግ ያስቸግራል። ይህ ሁኔታ የግዴታ በተለያዩ ፓርቲዎች መሀከል በሃሳብ ዙሪያ የሚደረግ ትግል እንዳይደረግ ስለሚያግድ ወደ መቃቃርና ወደ ጠባብ ስሜት የሚያመራ ይሆናል። ሽኩቻው የየግለሰቦችና ስልጣንን ለመጨበጥ የሚደረግ ትግል ስለሚሆን የአንድን ህብረተሰብ ዕድገት የሚቀጭ ይሆናል። በአብዮቱ ወቅት የተከሰተው ሁኔታ የሚያረጋግጠው ጥቂት ግለሰቦች የራሳቸውን ጥቅም በማስቀደማቸውና በሃሳብ ዙሪያ የሚደረገውን ትግል ቦታ ስላልሰጡት ነው። በህብረተሰብ ሳይንስ ላይ ከተመረኮዘ ክርክር ይልቅ ችግሮችን በጠብመንጃ መፍታት አለብን፣ እንችላለንም ብለው በመነሳታቸው ነው። የአገርንና የብዙ ሚሊዮንን ህዝብ ዕድል ቅድሚያ ከመስጠት ይልቅ በስልጣን ጥም በመታወራቸው የብዙ መቶ ሺህ ህዝብ ደም መፍሰሱ ብቻ ሳይሆን የሁለትና የሶስት ትውልድ ዕድል እንዲጠፋ አደረጉ። እንደዚህ ዐይነቱ ሁኔታ እንዳይደገም ከተፈለገ ወደ ፊት የሚፈጠሩ ፓርቲዎች በዕውነተኛ ፍልስፍና ላይ የተመሰረተን አርቆ አስተዋይነትን የትግል መመሪያቸውና የዕድገት መለኪያቸው ማድረግ አለባቸው ።

በአብዮት ወቅት የተፈጠሩት ድርጅቶች የማርክሲዝምን አርማ ያነገቡ ቢሆኑም፣ ከነዚህ ውስጥ በጥቂትም ቢሆን በቲዎሪው ውስጥ ያለፉት ሁለት ድርጅቶች ብቻ ናቸው። ሌሎች ግን አዲስ ከተፈጠረው ሁኔታ ጋር ራሳቸውን በማቀናጀትና የማርክሲዝምን ካባ በመልበስ ለግርግሩ ልዩ እምርታ ሰጡት። በካፒታሊስት ህብረተሰብ ውስጥ የተፈጠረው ቲዎሪ ደግሞ ከኢትዮጵያ ሁኔታ ጋር ለማቀናጀት ከፍተኛ የጭንቅላትን ስራ የሚጠይቅ ነበር። በሌላ ወገን ግን፣ ቲዎሪዉን እስከተወሰነ ደራጃ ብቻ ነው የአንድን ህብረተሰብ ሁኔታ ለመተንተን ስራ ላይ ማዋል የሚቻለው። የማርክሲዝም ቲዎሪ የአንድን ህብረተሰብ የማሰብ ኃይል የዕድገት ደረጃ ቁጥር ውስጥ ሰለማያገባ፣ ቲዎሪውን የተቀበሉ ታጋዮች ከሃሳብ ትግል ይልቅ ወደ መሳሪያ ትግል እንዲያዘነብሉ ይገደዳሉ። ይህ በማቴሪያሊስት ቲዎሪ ላይ የተመሰረተው ትንተናና አመለካከት ደግሞ የግዴታ በእነ ፕላቶንና በኋላም በጀርመን ክላሲኮች የዳበረውን በሃሳብ ዙሪያ የሚደረግ ውይይትና ከዚያም የሚፈልቀውን ፖሊሲ የሚቃረንና የነገሮችን ሂደት ገልብጦ እንዲያይ የሚያደርግ ነው። አንድ ህብረተሰብ የማሰብ ኃይሉን እያዳበረና አርቆ አስተዋይነትን የዕውቀት ምንጭ በማድረግ መሳሪያዎችን በመፍጠርና ቆንጆ ቆንጆ ነገሮችን እየሰራ ወደ ህብረተሰብአዊ ስምምነት እንዲያመራ የሚያግዝ አይደለም ማለት ነው። ቲዎሪው የብዙ ነገሮችን ተስማምቶ መኖር የሚቃወም የሚመስልና፣ በአንድ ህብረተሰብ ውስጥ የተለያዩ ነገሮች በቅራኔ ህግጋት መሰረት ተስማምተው ሊኖሩ እንደማይችሉ ስለሚያስመስል ብዙዎችን ሊያሳስት ይችላል ። በዚህም ምክንያት ነው ቲዎሪዉ ተግባራዊ ሊሆን በተሞከረባቸው አገሮች ሁሉ ከሊትሬችር እስከ ሙዚቃ ድረስና እስከ ህንጻ አሰራር ድረስ አንድ ወጥ በማድረግ በግሪክ ስልጣኔ የዳበረውን የስምምነት(Harmonious) የህንጻ አሰራርና የዕድገት ፈለግ ተግባራዊ እንዳይሆን በር የዘጋው። በዚህም ምክንያት በአገራችን የተፈጠሩት ፓርቲዎችም ሆነ ድርጅቶች ይህንን ሁሉ ሳያጤኑ -ኃይሎች አልነበሩም ማለት አይደለም- ወደ ማያስፈልግ ሽኩቻ ውስጥ የገቡት።

ዛሬም በፓርቲዎች መሀከል ያለው መሻከርና አንደኛው የሌላውን ዐይን ለማየት ፈቃደኛ ለመሆን አለመፈለግና አብሬ አልሰራም ማለት ቲዎሪንና ፍልስፍናና እንዲሁም ደግሞ ሃሳብን የትግል መመሪያ ለማድረግ ካለመቻል የተፈጠረ ሁኔታ ነው። በዚህም ምክንያት ደርጅቶችም ሆነ አመራሮቹ የታሪክን አደራ ሊሸከሙ የማይችሉ እየሆኑና አባሎቻቸውን በጠባብ ክልል ውስጥ ብቻ እንዲሽከረከሩ በማድረግ ለዕድገት የሚሆነውን የሃሳብ ልውውጥ በር እየዘጉ ነው። ይህ እጅግ ጎታች ሁኔታ ካልተሰበረና በአዲስ ኃይል ካልተተካ የኢትዮጵያ ህዝቦች ዕድል ለብዙ መቶ ዐመታት ተንጠልጥሎ እንዲቀር ይገደዳደል ማለት ነው። ከዚህ ስንነሳ፣ ከግንቦት 1977 ዐመተ ምህረት በፊት የተመሰረቱት ፓርቲዎችና በኋላም ወደ ጣምራነት ያመሩትና ዛሬ ደግሞ ስማቸውን ለውጠው የሚንቀሳቀሱት ፓርቲዎች ታሪካዊ ሚና እጅግ አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ እንደገባ መገመት ይቻላል። በአንዳች አጋጣሚ ስልጣን ቢይዙ እንኳ ህዝብን አስተባብሮ ታሪክን የመስራት ኃይላቸው የመነመነ ይሆናል ማለት ነው። በብዙ የአፍሪቃ አገሮች በምርጫ ስም የተከሰቱትና አሁንም ቢሆን ድህነትን ያስፋፈቱትና ህዝብን የሚያተራምሱት ሁኔታዎች በአገራችን ምድር ላይም የግዴታ ይከሰታሉ ማለት ነው።

ወደ ነፃ አውጭ ደርጅት ነን ወደ ሚሉት ጋ ስንመጣ ደግሞ ከዚህ የባሰ እጅግ አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ እንገባለን። በተለይም እንደ ኦሮሞ ነፃ አውጭ ድርጅት(OLF) የመሳሰሉት ትግላቸውና እንቀስቃሴቸው በምንም ፍልስፍና ላይ የተመሰረተ አይደለም። የህብረተሰብን ህግና ሎጂክ የተከተለ አይደለም። ጭቆናና ቅኝ-ግዛት የሚለውን መፈክር

ከጠቅላላው ህብረተሰብአዊ ዕድገት ነጥሎ በማውጣትና ቅስቀሳ በማድረግ የተፈጥሮን ህግ የሚጥስና የአንድን ትውልድ አመለካከት በቁንጽል አስተሳሰብ ላይ እንዲያተኩር በማድረግ ህብረተሰብአዊ ውዝግብን የሚፈጥር አካሄድ ነው። የሰዎችን መሰረታዊ የመኖር ፍላጎት ፣ መብላት ፣ ንጹህ ውሃ ማግኘት ፣ መጠለያና እንዲሁም ሌሎች መሰረታዊ ነገሮች እንዳይሟሉ የሚያደርግና ህልማቸው ለብዙ መቶ ዐመታት ተንጠልጥሎ እንዲኖር የሚያደርግ አደገኛ የትግል ስልት ነው። ዕውነተኛ ስልጣኔን የሚቀናቀንና ርስ በርሱ የሚጋጭ ትግል ነው። ትግሉ ፀረ-አሮሞና ፣ በአጠቃላይ ሲታይ ፀረ ሰው ነው። ሰብአዊነትን የሚቃወምና የሰዎችን ተፈጥሮአዊ የፈጠራ ችሎታን የሚያፍን ነው።

ጭቆናና ቅኝ ግዛት የሚለውን ፅንሰ-ሃሳቦች ጠጋ ብለን ስንመለከት ፣ ድሮም ሆነ ዛሬ ጭቆና ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል የሚመለከት እንጂ ፣ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ አንድን ብሄረ-ሰብ ከመጀመሪያውኑ ለማጥቃት የተወሰዱ የርዕዮተ-ዓለምም ሆነ የፖለቲካ እርምጃዎች አልነበሩም። ቢኖሩ ደግሞ አንዳንድ አፈንጋጭ ኃይሎች እንቅስቃሴ ሲያደርጉ መደረግ የሌለባቸው እርምጃዎች ተወስደዋል። ይህ ዐይነቱ ዕርምጃ በብዙ ብሄረ-ሰቦች ውስጥ የተካሄደና በጊዜው ከነበረው ንቃተ-ህሊናና የፖለቲካ ስሌት ተነጥሎ ሊታይ የሚችል አይደለም። በዚህም መሰረት አንዱን ብሄረ-ሰብ የሚጠቅም የኢኮኖሚና የህብረተሰብ ፖሊሲ በአፄውም ሆነ በደርግ ዘመን ተካሂዶ በፍጹም አያውቅም። በካፒታሊዝም አፍላ ዘመን ከሰሜኑ ግዛት ይልቅ ፣ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ የሚታይበት የኦሮሞ ኤሊት ዛሬ ግዛቴ ነው እያለ የሚዘባነንበት የደቡቡ ክፍል ነው።

ወደ ቅኝ ግዛት የሚለው ጽንሰ-ሃሳብ ስንመጣ ፣ ራሰን ከሌላው የኢትዮጵያ ግዛት ከልሎና አጥሮ የኖረ ፣ የራሱ ባንዲራና ገንዘብ የነበረውና በስራ-ክፍፍልም የዳበረ ፣ እንዲሁም ደግሞ መንግስታዊ መዋቅር የነበረው የኦሮሞ ግዛት አልነበረም። ኦሮሞዎች በታሪካቸው ከብት እያረቡ የሚኖሩና ፣ ምናልባትም ከአርሲ ፈልሰው በመነሳት ቀስ በቀስ ሌላውን የኢትዮጵያ ግዛት ያዳረሱ ናቸው። በአስራ ስድስተኛው ክፍለ-ዘመን ወደ ሌላው ግዛት ሲስፋፉ ከነሱ የተሻሉ በስራ-ክፍፍል የዳበሩ እንደ ሃድያና ከምባታዎች እንዲሁም የሰሜኑ ግዛት ጋር ይጋጫሉ። የነዚህን የህብረተሰብ ክፍሎች የዳበረ የስራ-ክፍፍልና መንግስተ-መዋቅር በመደምሰስ ፣ በነሱ አባባል እነዚህን የግዛት ክልል ቅኝ-ግዛት ያደርጓቸዋል። ይህ ደግሞ የሚገርም ነገር አይደለም። በዓለም ታሪክ ውስጥ የታየ ነው። ከአንድ ቦታ የፈለቁ ህዝቦች ወይም ጎሳዎች ሌላን ቦታ በመውረርና በመስፈር ኑሮአቸውን እዚያው ማደላደል ይጀምራሉ። የስራ-ክፍፍልን በማዳበር ከዝቅተኛው ወደ ከፍተኛው የህብረተሰብ ክፍል በመሸጋገር እንደ ንቃተ-ህሊናቸው ለአዲሱ ግዛታቸው ልዩ መልክ ይሰጡታል። በዚህ መልክ ነው በብዙ የአውሮፓ አገሮች ህብረ-ብሄሮች(Nation-States) የተመሰረቱት። ይህ ደግሞ ከታች ወደ ላይ የተካሄደ እንቅስቃሴና ህብረተሰብአዊ ዕደገት እንደመሆኑ መጠን ይህንን የዕድገት ሁኔታ ለመቀልበስ መሞከር የተፈጥሮን ህግ እንደ መጣሰ ይቆጠራል። ኤክሰኖፋነሰ(Xenopahnes) የተባለው የግሪክ ፈላስፋ የሰው ልጅ በዕድገቱ ወስጥ ያደረገውን ውጣ ውረድና መሻሻል በመመርመር ፣ ከቆመበት በመነሳት ወደፊት መገስገስ እንዳለበት ያመለክታል። ***“ Man, marching on from the place where he finds himself and laying out his own path, faces forward and not backward. He fixes his eye not on the distance already covered but on the ground still to be covered.”*** በመሆኑም የኦሮሞ ብሄረ-ሰብ አንዳንድ የኦሮሞ ኤሊቶች እንደሚመኙት ወደ ኋላ ተመልሶ የጋዳን ስርዐት ልመስርት እያለ ጊዜውን የሚያቃጥልብት ምክንያት የለውም። እንደዚህ እያሉ የማይሆን ቅስቀሳ ማስፋፋትና ቀድሞ አማራ ፣ ዛሬ ደግሞ ትግሬ እየገዛን ነው እያሉ መዋሸትና ጥላቻ መቀስቀስ ወደ ማያስፈለግ ግብግብ እንደማምራት ይቆጠራል። የጋዳን ስርዐት እንደገና መመስረት አለብን ማለት የታሪክን ጎማ ወደ ኋላ ማሽከርከር ብቻ ሳይሆን ፣ ከቪላ ቤት ወጥቼ የግዴታ ሳር ቤት መኖር አለብኝ እንደማለት የሚቆጠር የቂሎች የትግል ዘዴ ነው። የኤና የአባብያ እንዲሁም አቶ ሌንጮ አልያስ ዮሐንስ ህልምና እንዲሁም ዛሬ ሺህ በሺህ የሚቆጠሩ ስማቸውን ወደ አባነት የለወጡ ትግል መሆን ያለበት ፣ እንዴት አድርገን ተባብረን ሰላም ፣ ፍቅርና ብልጽግና የሰፈነባት ህብረተሰብ ልንመሰርት እንችላለን እያሉ ማውጣትና ማውረድ ነው። ከዚህ ውጭ የሚደረግ ትግል ሁሉ የኦሮሞን ብሄረ-ሰብ የተፈጥሮ መብትና ፍላጎት የሚፃረር ነው። *ማንኛውም በኢትዮጵያ ግዛት የሚኖር ብሄረ-ሰብ ሁሉ ፣ የትግሉ አርማ ውድ ወንድማችን አቶ አባንግ እንደሚያስተምረን ፣ ሰብአዊነትን ከጎሳ ፖለቲካ በማስቀደም ለአዲሲቱ ኢትዮጵያ መታገል ብቻ ነው።*

ስለዚህም ከገባንበት ውዥንብር ለመውጣትና ሌላም አደጋ እንዳይከሰት የምንፈልግ ከሆነ ፣ ሳንፈራና ሳንቸር በሃሳብ ዙሪያ በጥሞናና በመከባበር መወያየትና መከራከር አለብን። ስለሆነም ፣ ቀስ በቀስ ወደ ሌሎች ጠለቅ ያሉ ሃሳቦች ከማምራታችን

በፊት ለምን ዐይነት ህብረተሰብ ነው የምንታገለው ? እንዴትስ የተራጋጋ ህብረተሰብ ለመመስርት እንችላልን? ወደ ሚለው መሰረታዊ ሃሰቦች ላይ መወያየት ለገባንበት ጭንቀት ለጊዜውም ቢሆን የተወሰነ መልስ ሊሰጥ ይችላል ብዬ አምናለሁ።

## ለምን ዐይነት ህብረተሰብ ነው የምንታገለው ?

ከመጀመሪያውኑ መታወቅ ያለበት ጉዳይ የምንፈልገውን ህብረተሰብ በሃሳብ ደረጃ ማውጠንጠንና በወረቀትም ላይ መንደፍ እንችላለን። ወደ ምንፈልገው ህብረተሰብ ለማምራት ግን በብዙ ሁኔታዎች ነው የሚወሰነው። ወደፊት እንደዚህ ያሉ ነገሮች ሊከሰቱ ይችላሉ ብሎ በእርግጠኝነት መናገር ባይቻልም ፣ አሁን ያለንበት ንቃተ-ህሊናና ተጨባጩ ሁኔታዎች የወደፊቱን ዕድላችንን ይወስናሉ። ስለዚህም ፣ ወደ ምንፈልገው ህብረተሰብ ለመድረስ ምን ምን እርምጃዎች ብንወስድ ይሻላል ብለን ብንወያይ የተወሰነ መልስ ልናገኝ እንችላለን። በመጀመሪያ ግን አንዳንድ መሰረተ-ሃሳቦችን ግልጽ ማድረግ ያስፈልጋል።

የአገራችንንም ሆነ የብዙ አፍሪቃ አገሮች የህብረተሰብ አወቃቀር ለተለመከተ ሰርዓት የሌለውና ሎጂክን የተከተለ አይደለም። ዝም ብሎ በአቦሰጡኝ የተመሰረተ ነው የሚመስለው። ወደ አውሮፓ ስንመጣ ግን ፣ ከግሪክ ፍልስፍና የተወሰደው የተስተካከለ ህብረተሰብአዊ አገነባብና የከተማዎች ዕድገት የሰዎችን የማሰብ ኃይልና እያንዳንዱ የህብረተሰብ ክፍልም የራሱን ሚና እንዲረዳና በህብረተብ የስራ-ክፍፍል ውስጥ እንዲሰማራ ሊያደርገው በቅቷል። በዚህ ላይ ፣ ከአስራ አምስተኛው ክፍለ-ዘመን ጀምሮ ብቅ ያለው ፣ ባህል ያለው የከበርቴ መደብ ታሪክ ሰሪ በመሆን የግንባር ቀደምትነት ሚናን እየተጫወተ መጣ። የከበርቴው መደብ በምርት ብቻ ሳይሆን ፣ የክላሲካል ህንፃ ስራዎች ፣ የስዕልና የክላሲካል ሙዚቃ ፈጣሪዎችን በገንዘብ ደጋፊ በመሆን ህብረተሰቡ እንዲተሳሰር ከፍተኛ ሚና ሊጫወት በቅቷል። ከ16ኛው ክፍለ-ዘመን ጀምሮ እያደገ የመጣው የፍጹም ሞናርኪ አገዛዝና የአገር ውስጥ ገበያን ለማደበር የተወሰደው የመርካንታሊስት የኢኮኖሚ ፖሊሲ የህብረ-ብሄርን(Nation-State) አገነባብ ሊያፋጥነው ችሏል። ይህ ሁኔታ የህዝቡን አመለካከት በመለወጥና ወደ አንድ አማካይ ማዕከል እንዲያተኩር በማድረግ ብሄራዊ ስሜቱን ለማዳበር ችሏል። ***አገር ፣ ህብረተሰብ ፣ ብሄራዊ-ስሜትና ብሄራዊ ኢኮኖሚ አንድ ላይ ተያይዘው የሚሄዱና ቀስ በቀስም ጠቅላላውን ህብረተሰብና አገር ያዳረሱ ለመሆን በቅተዋል።*** በየታሪክ ወቅት የተከሰቱትን ውጣ ውረዶችንና የእርስ በርስ መተራረዶች ትተን ፣ የአውሮፓ ህብረተሰብ አወቃቀር ሎጂክን የተከተለ ነው ማለት ይቻላል። ዝም ብሎ ተራ የገበያ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የተካሄደበትና የሚካሄድበት ብቻ አይደለም። ባህላዊ ፣ ፓለቲካዊ ፣ እሴታዊ ፣ ጥበባዊና ልዩ ልዩ ነገሮች የሚካሄዱበት ማህበረ-ሰብ ነው ማለት ይቻላል።

ወደ ኢትዮጵያ ስንመጣ ከላይ የተጠቀሱት ለአንድ ህብረተሰብ መዳበርና ለተከታዩ ትውልድ እንዲተላለፍ ለማድረግ የሚያስችሉ መሰረቶች ሊጣሉ አልቻሉም። የከተማዎችና የመንደሮች በስነ-ስርዓት አለመሰራት ፣ ሙዚየሞችና የቲያትር ቤቶች በአገሪቱ ምድር አለመቋቋምና አለመስፋፋት ፣ ለጭንቅላት መዳበር የሚጠቅሙ ቤተ-መጻህፍቶች አለመስፋፋት ፣ የስፖርትና የባህል ማዕከሎች አለመቋቋም ፣ ልዩ ልዩ ህበረተሰብአዊ መዋቅሮች(Social Network) አለመኖር ፣ ህብረተሰቡ ተዘበራርቆ እንዲኖር አስገደደው። የሻይ ቤቶችና የሴተኛ አዳሪ ቤቶች እንዲሁም ዲስኮ ቤቶች መስፋፋት አዲሱን ትውልድ የቆሻሻ ባህል ሰለባ ሊያደርገው በቃ። ከ1940ዎቹ መጨረሻ ጀምሮ የተፈጠረው ልቅ የሆነ ህብረተሰብአዊ አወቃቀርና የኢኮኖሚ ፖሊሲ የግዴታ ማጅራት መቺዎችን ፣ ውሽታሞችን ፣ ሌቦችንና ከሀዲዎችን በመፍጠር የህብረተሰብአችን ዕድገት እንዲዛነፍ አደረገ። ዛሬም ያለው ሁኔታ ይህንን የሚመስል ወይም ከዚህ የባሰና በመንግስት ደረጃ ውስጥ ለውስጥ የሚደገፍ ነው። ስለሆነም ፣ አዳዲስ የህብረተሰብ ኃይሎች ብቅ የሚሉት በአፈጣጠራቸው እንደዚህ ሆነው ሳይሆን ፣ ባለማወቅ የተዋቀረው ህብረተሰብአዊ ሁኔታ ስለሚያሰገድዳቸው ብቻ ነው። በዚህም ምክንያት ፣ የኢትዮጵያ ህብረተሰብ እስካሁንም ድረስ የታሪክን አደራ ሊሸከም የቻለ የህብረተሰብ ክፍል ማፍለቅ አቅቶት ሲንገዳገድ ይታያል። የዕድገቱ መዛባትና የህብረተሰቡ መዘበራረቅ ለአፈንጋጭና ለፀረ-ዕድገት ኃይሎች በር በመክፈት የህዝቡ አትኮሮ አንድ እንዲሆንና ለዕድገት እንዳይነሳ አንቆ ይዞታል። በተለያየ የፓርቲ ስምና የጎሳ ፖለቲካ የተጠመዱ ኃይሎች ከዚህ ወይም ከዚያኛው የውጭ መንግስት ጋራ በማበርና በመቆላለፍ የታሪክን ሂደት በማጣመምና ውዥንብር በመንዛት የስልጣኔው ጥማት እንዲረዝም አድረገዋል። ዛሬ አገራችን ያለችበት አስቸጋሪ ሁኔታ እንደዚህ ዐይነቱ የህብረተሰብን ግንባታ ሊረዳና ህብረተሰብ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ሊገባው የማይችል ሺህ በሺህ የሚቆጠር እዚህና እዚያ የሚጮህ ፖለቲከኛ ባይ ነን ደርጅቶች እንደ አሸን በመፍለቅ የፖለቲካውን አየር በማመቃቸው ነው። ከዚህ

ስንነሳ ፣ በአንድ በኩል የኢትዮጵያን ባንዲራ አንግበው የሚንቀሳቀሱ ፓርቲዎችና ፣ በሌላ ወገን ደግሞ ራሳችንን እንችላለን ብለው የሚራወጡ ድርጅቶች ከህብረተሰብ ግንባታና ከብሄራዊ ኢኮኖሚ አንፃር ፍላጎታቸውና ሚናቸው ምን እንደሆን ግልጽ አይደለም። በምን ፍልስፍናናና የኢኮኖሚ ፖሊሲ ርስ በርሱ ሊተሳሰር የሚችል ህብረተሰብ ሊመሰርቱ እንደሚችሉ እስካሁን ድረስ አላስረዱንም። ይህ ግልጽ እሳካልሆነ ድረስ ዘለዓለማችንን እየተደናበርን እንከርማለን ማለት ነው። ምክንያቱም ለአንድ ህብረተሰብ መገንባት የግዴታ ሳይንስና ፍልስፍና ሊታለፉ የማይችሉ መሰረተ-ሃሳቦች በመሆናቸው ነው።

## ብሄራዊ ኢኮኖሚን የመረዳት ችግር !

በብዞዎቻን መሀከል ያለው ትልቁ ችግር ህብረተሰብና ብሄራዊ ነፃነት የሚሉት ጽንሰ-ሃሳቦች በሀሳብ ዙሪያ መብላላት ያለመቻላቸው ነው። በተለይም ደግሞ ኢኮኖሚ የሚለው ትልቅ የአገር መገንቢያ መሳሪያ ወደ ንግድና ወደ ተራ የፍጆታ ምርት ክንዋኔ መለወጡ ለብሄራዊ-ኢኮኖሚ የሚደረገው ትግል ፈሩን እየሳተና ብዙ ወጣቶችን እያሳሳተ ነው። በነዚህ ሶስት መሰረታዊ ነገሮች ላይ ግልጽነት ከሌለ ደግሞ ትግለቻን ሁሉ ወሃ ቢወቅጡት እምቦጭ እንደሚሉት አነጋገር ይሆናል ማለት ነው።

በመጀመሪያ ደረጃ ስለ ኢኮኖሚ ሲወራ ፣ ከፕላቶን ጀምሮ እስከ አርሰቲቶለስና እስከ ማዕከለኛው ዘመን ድረስ በነበሩ ምሁራን የተደረሰበት ስምምነት ፣ ለአንድ ህብረሰተብ መተሳሰር የግዴታ የስራ-ክፍፍል መኖር እንዳለበት ነው። ሁለተኛ ፣ የግዴታ እንደዚህ ዐይነቱ የአንድን አገር ህዝብ ውስጣዊ መተሳሰር ሲያጠነክር ፣ በዚያውም መሰረት የአገር ውስጥ ገበያ (Home Market) ይዳብራል ማለት ነው። ከዚህ ጋር ተያይዞ ከተማዎች ሲያድጉና ሲበለጽጉ የሰው የማሰብና የመፍጠር ኃይል ከፍ ይላል። ከተራ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ አልፈው ቴክኖሎጂዎችንም በማዳበር ከማንኛውም አደጋ የሚከላከሏቸውን መሳሪዎች መስራት ይችላሉ። ለዚህ ደግሞ ሳይንስና ቴክኖሎጂ እጅግ አስፈላጊ መሰረተ-ሃሳቦች ናቸው።

ከ1880 ዓ.ም ጀምሮ የፍጆታን አጠቃቀምን ያሰቀደመው የማርጂናሊሰት ወይም የኒዎ-ለበራል ኢኮኖሚ ነገሮችን ሁሉ በጭንቅላታቸው በመገልበጥ አገሮች ረጋ ብለው የራሳቸውን ዕድገት እንዳይቀየሱ አገዳቸው። ይህ የተቆነጸለ የኢኮኖሚ መመሪያ በጭንቅላታችን ውስጥ ሰርጸ በመግባት አንድን አገር እንደ ህብረተሰብ ለመመስረት ፣ ቀስ በቀስ ምን ምን እርምጃዎች መከተል እንዳለበን ተምታታብን። ሁሉ ነገሮች በጠያቂና በአቅራቢ ፣ በተመጠነ ሀበት(scarce resources) ዙሪያ ሰለሚታዩ አገርን ለመገንባት በሚያሰፈልጉ መሰረታዊ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ላይ ርብርቦሽ ሳይደረግ ቀረ። የትምህርት ዘረፉ በኒዎ-ሊበራል ኢኮኖሚስቶች በመያዙ ሌላ የተሻለ ለአገር ግንባታ የሚያገለግል የኢኮኖሚ ቲዎሪ ማዳበር አልተቻለም። በዚህም ምክንያት ፣ የኢኮኖሚ ፖሊሲዎቹ ሁሉ የአገር ውስጥ ገበያ ለማዳበር የሚያስችሉ መሳሪያዎች አልነበሩም። ለምሳሌ ፣ በ1950ዎቹ ዐመታት የሲጋራና የኮካኮላና እንዲሁም የብስኩትና ሌሎች መጠነኛ ፋብሪካዎች ሲቋቋሙ በእርግጥስ በዚህ አማካይነት ህብረተሰብአዊ ለውጥና የቴክኖሎጂ ምጥቀት ሊመጣ ይቻላል ተብሎ በማመን ነው? የዚያን ጊዜው ፖሊሲ ካለምንም አርቆ አሳቢነትና ሳይንሰ-አልባ ውጭ በመካሄዱ ዛሬ ለተጋለጥነበት ሁኔታ አንደኛው ምክያንት ሊሆን በቃ። ዛሬም አንዴ በተቅዋም ፖሊሲ ፣ ሌላም የዐለም ንግድ ድርጅት ውስጥ ካልገባን በማለት መንደፋደፍና ፣ የኮሞዲቲ ገበያ አቋቁሞ የህብረተሰቡ አትኩሮ ከምርት ክንውንና ከቴክኖሎጂ ይልቅ በማጭበርበር ላይ እንዲመሰረት ማድረግ የቱን ያህል የኒዎ-ለበራል ኢኮኖሚ ፖሊሲ ጭንቅላታችን ውስጥ እንደገባና በመደናበር ላይ እንደመንገኝ ነው የሚያረጋግጠው።

ከዚህ ስነነሳ ፣ ለአንድ ህብረተሰብ ግንባታ ከመጀመሪያውኑ የገበያ ኢኮኖሚ ፖሊሲ እንደ መሳሪያ ሊቀርብ አይችልም። በታሪክ ውስጥም የገበያን ኢኮኖሚ መመሪያ አድርጎ አንድ ጠንካራ ህብረ-ብሄር የመሰረተ አገር የለም። ሰለዚህም ፣ መሆን ያለበት መመሪያ በአንድ ጊዜ ሁሉኑም ነገር በሚለው ፍልስፍና መሰረት ወደ ህብረ-ብሄር ግንባታ ሊያመራ የሚያስችለንን ህብረተሰብአዊ እንቅስቃሴ ነው ማካሄድ ያለብን። ከግሪክ ስልጣኔ እስከ ሬናሳንስና እስከ 19ኛው ክፍለ ዘመን የተካሄዱት የአውሮፓ የኢኮኖሚና የህብረተሰብ ግንባታዎች በሙሉ ዝም ብለው ከንጹህ የገበያ ኢኮኖሚ አንፃር የተነደፉ አይደሉም ።ይህ ቢሆን ኑሮ ቆንጆ ቆንጆ ከተማዎች ባልተገነቡ ነበር። ሳይንስና ቴክኖሎጂዎች ባላደጉ ነበር። በአንዳንድ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚስቶች ዕምነት ለካፒታለሲት ኢኮኖሚ ዋናው መሰረት የግል ሀብት መኖር ነው የሚለው በጣም ተቆንጽሎ የቀረበ አስተያየት የሚያመለክተው የቱን ያህል የኢኮኖሚ ቲዎሪ ከህብረተሰብአዊ ግንባታ ተነጥሎ መታየት እንደ ጀመረ ነው።

የመሬት ግላዊ ሀብት መሆንና የካፒታሊሰት መደብ መፈጠር የታሪክና የህብረተሰብ ሂደት ውጤቶች ናቸው። በህግ ከላይ የሚወረወሩ አይደሉም። የካፒታሊስቱ መደብ በህብረተሰብ ታሪክ ውስጥ ከታች ወደ ላይ ተኮትኩቶ ያደገና ቀስ በቀስ የራሱን ጥቅም ለማስከበር ወደ ጥገና ለውጥ በማምራት ህብረተሰብአዊ ኃላፊነት ለመውሰድ የበቃ ነው። የመሬት የግል ሀብትነት በጉልበት የተካሄደ ሲሆን ፣ ከ17ኛው ክፍለ-ዘመን ጀምሮ በእነ ጆን ሎክ የፈለቀው የህግ የበላይነት የሚለው መመሪያ ህጋዊ የሆነበትና የአዲሱን የመሬት ከበርቴ መደብ የበላይነት ያረጋገጠበት ሁኔታ ነው። ስለዚህም ፣ በኢትዮጵያ ውስጥ ከታሪክ ጋር ያለተገናዘበ ከላይ ወደ ታች የሚወረውር ህግ ተግባራዊ ማድረግ አንችልም። የኢትዮጵያ ህዝቦችም ጭንቀት የገበያን ኢኮኖሚ የመመስረትና ያለመመስረት ጉዳይ አይደለም። የኢትዮጵያ ህዝቦች የዕለት ተዕለት ጭንቀት እንዴት አድርገን ቢያንስ አንድ ጊዜ እንኳ ምን ቀምሰን እናድራለን የሚለው ነው። ለዚህ መልስ ለመስጠት ደግሞ የግዴታ ከዚህ እልክ አስጨራሽ የገበያ ኢኮኖሚ መላቀቅ አለብን። ይህ ማለት ግን ግለሰብአዊ ድርጊትና በግለሰቦች የሚካሄድ የንግድ ልውውጥ አይኑር ማለት አይደደለም። በግል የሚቋቋሙና የሚንቀሳቀሱ ከበርቴዎች አይኑሩ ማለቴ አይደለም። በዕደ-ጥበብ ላይ ያተኮረ ትናንሽ አምራች ኃይል አይደግ ማለቴ አይደለም። ጥያቄው በመንግስትና በሎካል ደረጃ የተቀነባበረ ህብረተሰብአዊ ድርጊትን ከግለሰብአዊ ድርጊት ጋር በማጣመር እንዴት አደርገን ረሀብን እየተዋጋን ብሄራዊ ኢኮኖሚ መገንባት እንችላለን ነው። ስለዚህም ፣ ረሀብን ከኢትዮጵያ ምድር ለአንዴም ለመጨረሻም ጊዜ ለማውደም ትላልቅ ፕሮጀክቶችን ከትናንሽ ፕሮጀክቶች ጋር ማቀነባበር አለብን ማለት ነው። ይህም ማለት ሊሰራ የሚችል ሁሉ ፣ ሊሰሩ ይችላሉ በሚባሉት ፕሮጀክቶች ላይ በአንድነት ተነስቶ መረባረብ ሲችል ረሀብን ከኢትዮጵያ ምድር እናወድማለን። ድህነትን በ20 ዐመት ውስጥ አሁን ከላበት ሁኔታ በከፍተኛ ደረጃ እንዲቀንስ እናደርጋለን። ከ30-50 ዐመት ባለው ጊዜ ውስጥ ጠንካራ ብሄራዊ ኢኮኖሚ መገንባት እንችላለን። በዚያውም ፣ የኢትዮጵያን ስዕል እንዳለ መቀየር እንችላለን ማለት ነው። ይህ ሲሆን ከስህተታችን እየተማርን ቀስ በቀስ ከዝቅተኛ ወደ ከፍተኛ ደረጃ በመሸጋገር ለብሄራዊ ኢኮኖሚና ለጠንካራ ህብረተሰብ የሚሆነውን መሰረት መጣል እንችላለን።

ስለሆነም ፣ ሂደታችንና ዓላማችንም ሁሉ ንጹህ ገበያን መመስረት አለብን በሚለው ዙሪያ መሽከርከር የለበትም። አንድ ወጥ ህብረተሰብ ለመመስረት መቃጣት አደጋ እንደሚያስከትል ሁሉ ፣ በነፃ ገበያ ዙሪያ የሚሽከርከር ሃሳብና ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ የሚደረግ ሙከራ ከእጅ አይሻል ዶማ እንደሚሉት አነጋገር ይሆናል ማለት ነው። በሌላ አነጋገር ፣ የኢህአዴግን የገበያ ኢኮኖሚ የምንቃውም ከሆነ ከሱ ሺህ ጊዜ የሚሻል የኢኮኖሚ ፖሊሲ ይዘን መቅረብ አለብን ማለት ነው።

ከዚህ ስንነሳ በታሪክ ውስጥ እንደታየውና እንደተረጋገጠው የመጀመሪያው ተግባር ከውስጥ የራስን የሰውና የተፈጥሮ ሀብት ማንቀሳቀስ መቻል ቀናውና ፍቱኑ መንገድ ነው። ለዚህ ደግሞ ዋናው መሰረት ፖለቲካዊ አደረጃጀት ነው። ዲሲፕሊንና ስራን ማክበር ከማንኛውም በላይ መያዝና ተግባራዊ መሆን ያለባቸው መሰረተ-ሃሳቦች ናቸው። በታሪክ ውስጥ ስልጣኔዎች ሁሉ የተጀመሩትና ወደ ከፍተኛው ደረጃ የደረሱት በመጀመሪያውኑ በገንዘብ አማካይነት ወይም ገንዘብ ስላለ አይደለም። የሰው ልጅ ከእንስሳ የተሻለ በመሆኑ የግዴታ ስልጣኔን ማምጣት አለብኝ ብሎ በመነሳቱ ከባቢሎን እስከ ግብጽና ከዚያም እስከ ግሪክና ሮማውያን የመሳሰሉትን ስልጣኔዎች ተግባራዊ ማድረግ ቻለ። ለዚህ ዞሮ ዞሮ በፍልስፍና ላይ የተመሰረተ አመራር ያስፈልጋል። ስለዚህ ህልማችን ቆንጆ ፣ ሰላምና ብልጽግና የሰፈነባት አገር መመስረት አለብን በሚለው መሰረታዊ አስታሳሰብ ላይ የተመረኮዘ መሆን አለበት። ይህ በጭንቅላታችን ሰቋጠርና ተግባራዊ ለማድረግ ወደ ስራ ስንሰማራ ወደ ማይቀረው ዓላማችን ቀስ በቀስ ማማራት እንችላለን። አንድን አገር ለመገንባት በአንድ ትውልድ ሊጠናቀቅ የሚችል ጉዳይ አይደለም ። የሶስትና የአራት ትውልድን ትግል የሚጠይቅ ነው። ይህም ሊሆን የሚችለው አሁንም ቢሆን ከአሁኑ በትክልለኛ መመሪያ ስንመራ ብቻ ነው። ካለበሊዚያ ከሁለት መቶ ዐመት በኋላ ከመቃብራችንን ነቅተን አገራችን ስንመለከት እንዳስቀመጥናት ሆና ካየናት ቶሎ መቃብራችን ውስጥ እንመለስ ብለን አርፈን እንድንተኛ እንገደዳለን ማለት ነው። ይህ እንዳይሆን ከፈለግን ከአሁኑ ማሰብ አለብን።

## የብሄራዊ ነፃነትን ጉዳይ የመረዳት ችግር !

በብዙዎቻችን ዘንድ ስለ ህብረተሰብና ብሄራዊ ኢኮኖሚ የተዛባ አመለካከት እንዳለን ሁሉ ስለ ብሄራዊ ነፃነትም አመለካከታችን የተዛነፈ ነው። ቀደም ብዬ ባወጣሁት ጽሁፍ ላይ የአንድ አገር ብሄራዊ ነፃነት መገርሰስ አገር ተቆርሶ ስለተሰጠ ብቻ ግምት ውስጥ የሚገባ አይደለም። ስለ ብሄራዊ ነፃነት ሲወራ የቱን ያህል የውጭ ኃይሎች በአገራችን ምድር ፣ በተለይም በፀጥታና በሚሊታሪ መዋቅር ውስጥ በመግባት ህልውናችንን ይፈታተናሉም ማለት ነው። ባለፉት 60 ዐመታት በውጭ የስለላ ኃይሎች የተያዘው ፈሊጥ ፣ የራሳቸውን ሰዎች እየመለመሉ የሶስተኛውን ዓለም መንግስታት ህብረተሰብአዊ ተግባራቸውን እንዳይወጡ ማድረግ ነው። በዚህም አማካይነት ፣ አለመተማን በመፍጠር ህብረተሰብአዊ ቀውስ እንዲፈጠር አሻጥር መስራት ነው። ከዚህ ጋር ተደምሮ ፣ የምዕራብ አገሮችና አሜሪካ ያላቸውን የኢኮኖሚ ፣ የፖለቲካና የሚሊታሪ የበላይነት በመጠቀም ከ1945 ዓ.ም ጀምሮ ያቋቋሙትን የኢኮኖሚ ኢንስቲቱሽኑች ተገን በማድረግ የሶስተኛውን ዓለም መንግስታት በማስገደድ የማይሆን የኢኮኖሚ ፖሊሲ እንዲከተሉ በማድረግ አጠቃላይ ህብረተሰብአዊ ሀብት እንዳይዳብር ማድረግ ነው። ከዚህም በመነሳት አዳዲስ የኢኮኖሚ ኃይሎችን በመፍጠርና ከነሱ ጋር እንዲቆላለፉ በማድርገ በፐሮፌሰር አንድሬ ጉንደር ፍራንክ ፣ በታወቀው የዓለም ኢኮኖሚሰት አባባል ወደ ውስጥ ዱርዬ የከበርቴ መደብ ማፍራትና ሀብት ከውስጥ ወደ ውጭ የሚፈስበትን ሁኔታ ማመቻቸት ነው። በዚህ ምክንያት በላፈው 60 ዐመታት ከአፍሪቃ እስከ ላቲን አሜሪካ ድረስ እንደዚህ ዐይነት የህብረተሰብ ሁኔታ በመፍጠር ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች በተወሰኑ መስኮች ላይ ብቻ እንዲተኩሩ አደረጉ።

ከዚህም ስንነሳ አሜሪካንም ሆነ ሌሎች የምዕራብ አውሮፓ አገሮች ብሄራዊ ነፃነታችንን ሲቀናቀኑ ከርመዋል። በተለይም ያለፈው 18 ዐመት የሚያረጋግጠው ይህንን ነው። በእከክልኝ ልከክልህ ፖለቲካ የአገራችንን ህብረተሰብ ሁኔታ ማዘበራረቅና የስልጣኔውን ፍላጎት ማራዘም ነው። ይህ ጉዳይ በተለይ በላፉት 18 ዐመታት በተቋቋሙት ፖርቲዎች የተጤነበት አይመስልም። አሜሪካን ወዳጃችን ነው ፣ ፈረንጅ እኛን አያጠቃንም እየተባለ የዋህነት የተሞላበት የልምምጥ ፖለቲካ ሲካሄድ ከርሟል። ቢስማርክ የመጀመሪያው የጀርመን ብሄራዊ-መንግሰት ገዢ እንዳለው በሁለት ወይም ከዚያ በላይ አገሮች መሀከል ወዳጅነት የሚባል ነገር የለም። ያለውና የሚኖረው ግኑኙነት የጥቅም ግኑኙነት ብቻ ነው። ይህንን ሀቅ ስቶ ደረትን ከፍቶ መስጠት በቀጥታ ኑና አገሬን ቅኝ-ግዛት አድርጓት እንደማለት ይቆጠራል። ብዙዎቻችን ለኢትዮጵያ አንድነትና ነፃነት እንታገላለን የምንል የፖለቲካ ሰዎች ብሄራዊ ነፃነት የሚለው ፅንሰ-ሃሳብ ሁለንታዊ በሆነው መልኩ እስካልገባን ድረስ ዝም ብለን ነው የምንታገለው ማለት ነው። ይህ ማለት ግን የቡራ ከረዩ ፖለቲካ እናካሂድ ማለት አይደለም። አስተሳሰባችንን በማስፋትና ሹል በማድረግ ጥንቃቄ የተሞላበት ፖለቲካ እናካሂድ ማለት ነው። ምክንያቱም ለአንድ ህብረ-ብሄር መመስረት ፣ለብሄራዊ ኢኮኖሚ መገንባትና ለህብረተሰብ ዕድገት የግዴታ የብሄራዊ ነፃነት መከበር አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታ ስለሆነ ነው። መልካም ንባብ !!

ፈቃዱ በቀለ

fekadubekele@gmx.de